# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የውጪ ንግድ አፈፃፀምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት / 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ


ማውጫ ........ i

የክዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ማጠቃለያ (Executive Summery) ........ I

ክፍል አንድ ........ 1

መግቢያ ........ 1

የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አመሰራረት ........ 1

የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የንግድ ዘርፍ አላማ ........ 2

የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የንግድ ዘርፍ *ራዕይ* ........ 2

የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የንግድ ዘርፍ ተልዕኮ ........ 2

የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የንግድ ዘርፍ ዕሴቶች ........ 2

የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ስልጣንና ተግባር ........ 3

የቀድሞው የንግድ ሚኒስቴር አደረጃጀት እና የሰው ኃይል ........ 5

ድርጅታዊ መዋቅር ........ 5

የሰው ኃይል ........ 5

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ ........ 6

የኦዲቱ ዓላማ ........ 6

ለኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Audit Area) ........ 6

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ........ 7

የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ........ 7

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ........ 7

ክፍል ሁለት ........ 9

የኦዲት ግኝቶች ........ 9

2.1. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድን ለማሳደግ ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ  መልኩ እቅድ አዘጋጅቶ ተግባራዊ እያደረገ ስለመሆኑ፤ ........ 9

የውጪ ገበያ መዳረሻዎችን ለመለየት የሚያስችሉ ጥናቶች መጠናታቸውን በተመለከተ፤ ........ 9

አመታዊ የወጪ ንግድ እቅድ ሲዘጋጅ በወጭ ንግድ ላይ ባለድርሻ የሆኑ አካላትን ያሳተፈ መሆኑን በተመለከተ. 10

ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶችን በአይነትና በመጠን የሚያድጉበት ሥርዓት መኖሩን በተመለከተ፤ .................... 12

በወጪ ንግድ ዙሪያ በላኪ እና ገዥ ድርጅቶች መካከል የሚፈፀሙ ኮንትራቶች ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል መመሪያ በማውጣት አፀድቆ ተግባራዊ ማድረግን በተመለከተ፤ ................................ 16

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ ስምምነቶችን የሚፈራረምበት እና የሚያስፈፅምበት ስርአት መኖሩን በተመለከተ፤ ........................................................................................................................ 18

የወጪ ንግድ በላቀ ደረጃ ለማስፋፋት የሌሎች ሀገሮችን ልምድ ለመቅሰም የሚያስችሉ ጥናቶች መኖራቸውን በተመለከተ፤ ........................................................................................................................ 19

2.2 ሚኒስቴር መ/ቤቱ በወጪ ንግድ ላይ ለሚሳተፉ አካላት ድጋፍ፤ክትትል እና የጥራት ቁጥጥር የሚያደርግበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ እያደረገ ስለመሆኑ፤ ........................................................................ 21

የወጪ ንግድ ምርቶችን የሚልኩ ላኪዎች በአለም ገበያ በስፋት ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ድጋፍ እና ክትትል መደረጉን በተመለከተ፤ ........................................................................................................ 21

የወጪ ንግድ ለማጠናከር ከላኪዎችና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የውይይት መድረክ መኖሩን በተመለከተ፤ 23

ላኪዎች ባዘጋጁት የወጪ ንግድ ዕቅድ መሰረት ኮንትራት እንዲገቡ እና እንዲልኩ ክትትልና ድጋፍ መደረጉን በተመለከተ፤ ........................................................................................................................ 25

ወደ ውጭ አገር የሚላኩ የሀገሪቱ ምርቶች በዓለም ገበያ ታዋቂ እንዲሆኑ መለያ የንግድ ምልክት (ብራዲንግ) እንዲኖራቸው መደረጉን በተመለከተ፤ ................................................................................. 26

ወደ ወጪ የሚላኩ ምርቶችን ጥራታቸውን የጠበቁ ባለመሆናቸው ከገዢዎች ጋር አለመግባባት እየተፈጠረ መሆኑን በተመለከተ፤ ........................................................................................................ 27

የወጪ ንግድ ምርቶች ከአስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ በታች ሆነው በተገኙት ላይ እርምጃ የሚወሰድበት ስርአት መኖሩን በተመለከተ፤ ........................................................................................................ 30

የወጪ ንግድ ምርቶችን በትክክለኛ ዋጋ ስለመሸጣቸው ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት መኖሩን በተመለከተ፤31

ለላኪዎች የሚሰጠው የወጪ ንግድ ፈቃድ ለተሰጣቸው አላማ መዋላቸውን የሚቆጣጠርበት ስርዓት መኖሩን በተመለከተ፤ ........................................................................................................................ 32

2.4.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ መረጃ አያያዝ እና አሰረጫጨትን በተመለከተ ስርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ ስለመሆኑ፤ .................................................................................................... 34

ዘመናዊ የመረጃ አሰባሰብ፤ የመረጃ አስተዳደር እና አሰረጫጨት መመሪያ መኖሩን በተመለከተ፤ ................. 34

የላኪዎችና የገዥዎችን መረጃ (ፕሮፋይል) (አድራሻ) በየወቅቱ በማሻሻል ለላኪዎችና ለገዥዎች መሰራጨቱን በተመለከተ፤ ..... 35

የላኪዎችን የመደራደርና የመወሰን አቅም ለማጎልበት ወቅታዊና ታማኝ የሀገር ውስጥ እና የዓለም የገበያ ዋጋ ትንበያ፤ የተፎካካሪ አምራች ሀገራት የምርት ሁኔታ፣ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን ለሚመለከታቸው አካላት በየጊዜው እንዲደርሳቸው መደረጉን በተመለከተ፤ ..... 36

ክፍል ሶስት ..... 38

መደምደሚያ ..... 38

ክፍል አራት ..... 40

የማሻሻያ ሀሳቦች ..... 40

አባሪ-1 የቀድሞው ንግድ ሚኒስቴር ድርጅታዊ መዋቅር ..... 43

አባሪ-2 የውጪ ንግድ ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት ጀነራል የአሰራር ስርአት ስዕላዊ መግለጫ (System Description) ... 44

አባሪ-3 የኦዲት መመዘኛ መስፈርት ..... 45

አባሪ 4፡ መጠይቅ የቀረበላቸው ላኪዎችና የላኪ ማህበራት ስም ..... 50

# የክዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ማጠቃለያ

## (Executive Summery)

የወጪ ንግድ በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን ለሀገሪቱ እድገት እና ልማት ካለው አስተዋፅኦ አንፃር መሰረታዊ አላማዎች እና ግቦች ከተጣለባቸው ዘርፎች መካከል አንዱ ነው፡፡በመሆኑ የወጪ ንግድ አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ እየተሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ መረጃዎችን በመከለስ እና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ኃላፊዎችን ቃለ መጠይቅ በማድረግ ከዚህ በታች የታዩትን ዋና ዋና ግኝቶች እና የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ምርቶችን በአይነትና በመጠን ለማሳደግ የዘረጋው ስርዓት የሌለ መሆኑን፤
- በላኪ እና ገዥ ድርጅቶች መካከል የሚፈፀሙ ኮንትራቶች ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑን፤
- ላኪዎች የገጠማቸውን ችግር ለመፍታት የተዘጋጀ ስርዓት አለመኖሩን፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለላኪዎች የሚሰጠው የወጪ ንግድ ፈቃድ ለተሰጣቸው አላማ ማዋላቸውን የሚቆጣጠርበት ስርዓት የሌለ መሆኑን፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ ዘመናዊ የመረጃ አሰባሰብ፤የመረጃ አስተዳደር እና አሰረጫጨት መመሪያ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑን፤

በመሆኑም፡-

❖ በአገር አቀፍ ደረጃ በየአመቱ የሚታቀደው የኤክስፖርት እቅድ ከአቅራቢው ጀምሮ ሁሉንም የግል ሴክተሮች ተሳታፊ ያደረገ፣ ለዕቅዱ ተፈጻሚነት ግብአት የሚሰጡበትንና ዕቅዱን በባለቤትነት ይዘው ለትግበራው የበኩላቸውን አስተዋጽኦ የሚያደርጉበት ሁኔታ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊያመቻች ይገባል፡፡ይህንን በማድረግም ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶችን በአይነት፣ በብዛትና በጥራት ለማሳደግ የሚያግዝ አሳታፊ የሆነ እቅድ ሊዘጋጅ እና ለተፈጻሚነቱ ድጋፍ፣ ክትትል እና ቁጥጥር የሚያደርግበትን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- በአገሪቱ ውስጥ በወጪ ንግድ ላይ የተሰማሩ ላኪዎች ምርቶቻቸውን ለመላክ በላኪ እና ገዥ ድርጅቶች መካከል የሚፈፀሙ ኮንትራቶች ላይ የላኪዎቹም ሆነ የአገሪቱ ጥቅም መጠበቁን ለማረጋገጥ የሚያግዝ የህግ ማዕቀፍ እና ህጉን ለማስፈጸም የሚረዱ እና የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል መመሪያ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ ሊያወጣ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ለላኪዎች የሚሰጠው የወጪ ንግድ ፈቃድ ለተሰጣቸው አላማ መዋሉን ለመቆጣጠር የሚያስችል ስርዓት ሊኖር ይገባል፡፡ ይህንን ለመከታተል የሚያስችል ኤክስፖርት የሚያደርጉትን ድርጅቶች ለመከታተልና ለመቆጣጠር የድርጅቶቹ አድራሻ መረጃ ተደራጅቶና በየጊዜው ወቅታዊ እየተደረገ በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በሌሎች አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች ሊያዝ ይገባል፡፡
- አጠቃላይ የአገሪቱን የወጪ ንግድ መረጃን ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ ዘመናዊ የመረጃ አሰባሰብ፣የመረጃ አስተዳደር እና አሰረጫጨት ሥርዓት ዘርግቶ መ/ቤቱም ሆነ በወጪ ንግድ ላይ የተሰማሩ ባለድርሻዎች ተግባራዊ ሊያደርጉት ይገባል፡፡

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሀገራችንን የወጪ ምርቶች በጥራት፣ በተወዳዳሪ ዋጋና በሚፈለገው መጠን ለዓለም ገበያ በማቅረብ የገበያ ድርሻችንን በማሳደግ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ልማት የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ከፍ ለማድረግ በኤክስፖርት ዘርፍ ኢንቨስትመንትን የማሳደግ፣ የምርትና ግብዓት አቅርቦትን የማሻሻል፣ ማኒፋክቸሪንግ ዘርፉን አስተዋጽኦ ለማሳደግ ሁለገብ ድጋፍ መስጠት በተለይም የኢንዱስትሪ ፓርኮችን የማስፋፋትና አቅም ያላቸው አምራቾች ወደ ምርት እንዲሸጋገሩ የማስቻል፣ የአገር ውስጥ ባለሃብቶችን ወደ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ እንዲገቡ ማበረታታትና መደገፍ፣የገበያ መሠረት ልማትን የማጠናከርና የሎጂስቲክስ አገልግሎትን የማሳለጥና ውጤታማ የማድረግ፣ የገበያ አድማስ ለማሳደግ የሚያስችል የገበያ ማስፋፊያ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም እየተከናወነ ያለው የወጪ ንግድ አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፤ፈጣን እና ቀልጣፋ እንዲሆን ማድረግ ወሳኙ ተግባር ነው፡፡

## የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አመሰራረት

2. ቀድሞ የንግድ፣ኢንዱስትሪ እና ቱሪዝም ሚኒስቴር በመባል ይታወቅ የነበረው መ/ቤት የአገር ውስጥ ንግድ ሚኒስቴር፣ የውጭ ንግድ ሚኒስቴር፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና የቱሪዝም ኮሚሽን በሚል በአራት መ/ቤቶች ተከፋፍሎ እንዲዋቀር ተደርጎ ነበር፡፡ የአገር ውስጥ ንግድ ሚኒስቴር እና የውጭ ንግድ ሚኒስቴር እንደገና በ1983 ዓ.ም የንግድ ሚኒስቴር በሚል ስያሜ እንዲዋሃድ የተደረገ ሲሆን፣በ1987 ዓ.ም ደግሞ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጋር በአዋጅ ቁጥር 4/1987 በመዋሃድ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሚል ስያሜ እንዲደራጅ ተደርጓል፡፡ይህ መ/ቤት በ1994 ዓ.ም አስር ተጠሪ መ/ቤቶችን በስሩ ይዞ እንዲያስተባብርና እንዲመራ በአዋጅ ቁጥር 256/1994 በአዲስ መልክ ተደራጅቶ ነበር፡፡ ሆኖም እንደገና በአዋጅ ቁጥር 411/1996 የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በስሩ አምስት መ/ቤቶች ለእርሱ ተጠሪ ሆነው እንዲደራጁ ተደርጓል፡፡ እንደገና በአዋጅ ቁጥር 691/2003 የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሚል ስያሜ በጋራ ሲሰሩ የነበሩ የስራ ዘርፎች በሁለት ሚኒስቴር መ/ቤቶች በተናጥል እንዲደራጁ ተደርጎ የንግድ ሚኒስቴር መ/ቤት ለብቻው ተቋቁሟል፡፡ በድጋሜ በማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 916/2009 ተቋቁሟል፡፡

3. በአሁኑ ወቅት መሰረታዊ የዕቅድ ዓላማዎች፣የማክሮ ኢኮኖሚ እና የዋናዋና ዘርፎች ግቦችን፣የአቅም ግንባታና የመልካም አስተዳደር ተግባሮችን እውን ለማድረግ የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1097/2011 የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሚል ስያሜ በስሩ አስራ አራት መ/ቤቶች ለእርሱ ተጠሪ ሆነው እንዲደራጅ ተደርጓል፡፡

## የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የንግድ ዘርፍ አላማ

4. ዘመናዊ፣ ፍትሃዊና በውድድር ላይ የተመሠረተ የንግድ አሠራርና የግብይት ሥርዓትን በማስፈን፣ የዓለም አቀፍና አካባቢያዊ ትስስር አካል በማድረግ እና የውጭ ምንዛሪ ግኝትን በማሳደግ ዘርፉ ለኢኮኖሚ ዕድገት፣ለሥራ ዕድል ፈጠራና ለድህነት ቅነሳ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ማስቻል እና የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ነው፡፡

### የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የንግድ ዘርፍ ራዕይ

5. በ2017 በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ የንግድና ቀላል የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተፈጥሮ ማየት፡፡

### የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የንግድ ዘርፍ ተልዕኮ

6. አሰራርን ግልፅ፣ ተደራሽና ውድድር የሰፈነበት እንዲሆን በማድረግ፣ ፍትሃዊ ንግድ በማስፈንና ለሀገር በቀል ባለሃብቱ የላቀ አገልግሎትና ድጋፍ በመስጠት እና የዘርፉን የሰው ሀብትና የቴክኖሎጂ አቅም በማሳደግ፣ ውጤታማ የአሠራር ስርዓት በመዘርጋት የአምራቹን፣ የሸማቹንና የንግዱን ማህበረሰብ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፡፡

### የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የንግድ ዘርፍ ዕሴቶች

- ❖ በአሳታፊነት፣ በግልፅነትና በተጠያቂነት ማገልገል፣
- ❖ ለደንበኛ እርካታ ቅድሚያ ትኩረት መስጠት፣
- ❖ ኪራይ ሰብሳቢነትን መታገል፣
- ❖ በጋራ ተባብሮ የመስራት ባህልን ማሳደግ፣
- ❖ ለሀገር በቀል ባለሀብቱ ስኬት መትጋት፣
- ❖ ሁልጊዜም ለመማርና ለለውጥ ዝግጁ መሆን፤
- ❖ ለፈጣን የቴክኖሎጂ ሽግግርና ተጠቃሚነት መስራት፣
- ❖ ለአካባቢ ደህንነትና እንክብካቤ መቆም፣
- ❖ በቅንጅት መስራት፤

## የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ስልጣንና ተግባር

7. የአስፈፃሚ አካላት ስልጣንና ተግባርን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 መሰረት ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተሰጠ ስልጣንና ተግባር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- ❖ የንግድና ኢንዱስትሪ ልማትንና ተወዳዳሪነት በቀጣይነት የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችን ይቀርጻል፣ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
- ❖ የግል ዘርፉን ተሳትፎ ለማሳደግ የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል፣ለአፈጻጸሙም ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣
- ❖ የሀገር ውስጥ ንግድ እንዲስፋፋና ህጋዊ አሰራር እንዲሰፍን ተገቢነት ያላቸው እርምጃዎችን ይወስዳል፣በክልሎች መካከል የሚደረግ የንግድ ግንኙነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል ፣
- ❖ የሀገሪቱ የውጪ ንግድ የሚስፋፋበትን እና የሚጠናከርበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣
- ❖ በአገልግሎት፣በግብርና እና በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማሩ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ምርቶቻቸውን ለውጭ ገበያ እንዲያቀርቡ ከሌሎች ተቋማት ጋር በመቀናጀት አስፈላጊውን ድጋፍ የሚሰጥበት ስርዓት ይዘረጋል፣ተግባራዊ ያደርጋል፣
- ❖ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የውጭ ንግድ ግንኙነት ይመሰርታል፣የንግድ ስምምነቶችን በህግ መሰረት ይፈራረማል፣ያስፈጽማል፣
- ❖ የገቢና ወጪ ንግድ እቃዎችን ጥራት ይቆጣጠራል ፣ተፈላጊውን የደረጃ መስፈርት የማያሟሉ የንግድ እቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ ይቆጣጠራል፣
- ❖ የገቢና ወጪ እቃዎች በትክክለኛ ዋጋ ስለመሸጣቸው ወይም ስለመገዛታቸው ለማረጋገጥ የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል፣ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር ክትትል ያደርጋል፣
- ❖ ቀላል፣ወጪ ቆጣቢና በቴክኖሎጂ የተደገፈ የንግድ ምዝገባና ፍቃድ አገልግሎት ስርዓት ይዘረጋል፣
- ❖ የዋጋ ቁጥጥር ሊደርጋባቸው የሚገቡ መሰረታዊ የንግድ እቃዎችና አገልግሎቶችን ዋጋ እያጠና ለሚኒስተሮች ምክር ቤት ያቀርባል ፣ሲፈቀድም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፣
- ❖ የንግድ ዘርፍ ማህበራት ፣የሸማቾች ማህበራት ፣የኢንዱስትሪ፣የዘርፍ እና የሙያ ማህበራት እንዲቋቋሙ ያበረታታል፣የተቋቋሙትንም እንዲጠናከሩ ያደርጋል፣

- የአገሪቱ ህጋዊ ስነ-ልክ ሥርዓት ለመተግበር እንዲቻል አስፈጻሚ አካላትን ያስተባብራል፣
- አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ያላቸው የንግድ እቃዎችና አገልግሎቶች የደረጃውን መስፈርት ማሟላታቸውን ይቆጣጠራል፣በሌሎች አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች የሚሰራባቸውን አስገዳጅ ደረጃዎች በተቀናጀ መልኩ እንዲተገበር ያደርጋል፣
- የኢንዱስትሪ ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ ፖሊሲዎችን ፣ስትራቴጅዎችንና መርሃ ግብሮችን ያዘጋጃል ፣በሚመለከተው አካል ሲጸድቁም ተግባራዊ ያደርጋል፣
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ስትራቴጂካዊ ትኩረት በሚሰጣቸው ዘርፎች የአገሪቱን ምርቶች ለውጭ ገበያ በማቅረብ ረገድ የታቀደውን እድገት ለማምጣት የሚያስፈልጉ ጥናት እና ምርምሮች ያካሂዳል፣ይተገብራል፣
- በኢንቨስትመንት አዋጁ መሰረት የአገር ውስጥ ባለሀብቶች በኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት የሚሳተፉበትን ሁኔታዎች ያመቻቻል፣ በስሩ ያሉ ተጠሪ ተቋማት በዋናነት ለአገር ውስት ባለሀብቶች ድጋፍ እንዲሰጡ ለማድረግ ተገቢውን ስርዓት ይዘረጋል፣ያስፈጽማል፣
- የኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማትን ለማሳደግ የሚያስችል የቴክኖሎጂ መረጣ የማላመድና ማስረጽ ተግባራትን ፣የምርጥ ተሞክሮ መቀመር፣የቴክኖሎጂ ሽግግር ፣የክህሎት ልማትና አጠቃላይ የኢንዱስትሪ ልማት አቅም ግንባታ ስራዎችን ያመቻቻል፣
- የኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማትና ምርታማነትን ለማሳደግ ኢንዱስትሪዎች የኤክትቴሽን አገልግሎት፣የቴክኖሎጂ ፣የግብዓትና የግብይት እንዲሁም በአመራረት ረገድ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፣ውጤታማነታቸውንም ያረጋግጣል፣
- የኢንዱስትሪ ምርቶች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ ፣በዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የአቅም ግንባታ፣የምርምርና ስርጸት ስራዎች እንዲከናወኑ ስርዓት ይዘረጋል፣ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ለኢንዱስትሪ ዘርፍ አስፈላጊ ሆነውን የሰው ኃይል ፍላጎትና አስተማማኝ ግብዓት ለማሟላት የሚቻልበትን ስልት ይቀይሳል፣
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመስራት የግብዓት አቅርቦት ትስስር ስርዓት እንዲዘረጋ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ተግባራዊ ያደርጋል፣

- ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታቸው ጉልህ የሆኑ የገቢ ምርቶች በአገር ውስጥ ምርቶች ኢንዲተኩ ድጋፍ ያደርጋል፣ገበያው ሊያቀርባቸው ያልቻለውን ወይም እጥረት በሚታይባቸው ምርቶችና አገልግሎቶች ዘርፍ መንግስት የሚያቀርብበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣
- በአነስተኛ፣በመካከለኛ እና በከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች መካከል የተቀናጀ ትስስር እንዲፈጠርና ስኬታማ ሽግግር  እንዲከናወን የሚያስችል  የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣
- ኢንዱስትሪዎች በአካባቢ ጥበቃ የተቀመጡ መስፈርቶችን እንዲያሟሉ ድጋፍ ያደርጋል፣
- የአገሪቱን የንግድና ኢንዱስትሪ መረጃዎች  አሰባሰብ፣አደረጃጀትና አጠቃቅምን ያስተባብራል፣የተቀናጀ መረጃ ያደረጃል፣ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፡፡

## የቀድሞው የንግድ ሚኒስቴር አደረጃጀት እና የሰው ኃይል

### ድርጅታዊ መዋቅር

8. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚኒስቴር የሚመራ ሲሆን በሚኒስቴሩ ስር ሁለት ሚኒስቴር ዴታዎች ተጠሪ ናቸው፡፡ በተጨማሪም በሚኒስትሩ ስር አስር ዳይሬክቶሬቶች፣አንድ ጽ/ቤት፣አንድ ማዕከል እና አንድ ኮርፖሬሽን እንዲሁም በአንደኛው ሚኒስቴር ዴኤታ ስር ሦስት ዳሬክቶሬት፣ አንድ ጽ/ቤት እና አንድ ባለስልጣን መ/ቤት የሚገኙ ሲሆን በሁለተኛው ሚኒስቴር ዴኤታ ስር አምስት ዳሬክቶሬት፣ አንድ ጽ/ቤት፣ አንድ ባለስልጣን መ/ቤት እና አንድ ድርጅት ይገኛሉ፡፡

**ድርጅታዊ መዋቅሩ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ (1) ተያይዟል፡፡**

### የሰው ኃይል

9. የቀድሞው ንግድ ሚኒስቴር  ያለው የሰው ሀይል ብዛት 573 ሲሆን  ከዚህም ውስጥ የሴት ሰራተኞች ብዛት 228 (39.79%) እና የወንድ ሰራተኞች ብዛት 345 (60%) ነው፡፡ በዚህ ወቅት ያለው የሰው ኃይል በሙያ ሲገለፅ ፒኤች ዲግሪ ብዛት ወንድ1፣ ማስተርስ ዲግሪ ወንድ 32 (5.5%) ሴት 4 (0.6%) ድምር 36፣ ቢኤ ዲግሪ ወንድ 216 (37.6%) ሴት 108 (18.8%) ድምር 324፣ ዲፕሎማ ወንድ 36 (6.2%) ሴት 36 (6.2%) ድምር 72 እና ከዲፕሎማ በታች ወንድ 58 (10.1%) እና ሴት 80 (13.96%) በድምሩ 138 በጠቅላላው 573 ሠራተኞች  ይገኛሉ፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ

10. የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን ከመንግስት ከሚመደብ በጀት እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚሰበስበው የንግድ ፈቃድ የአገልግሎት ገቢ ሲሆን የቀድሞው ንግድ ሚኒስቴር ከ2008 እስከ 2010 በጀት ዓመት የተመደበለትን በጀትና ከ2008 እስከ 2010 በጀት ዓመት ድረስ የወጣው ወጪ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

| በጀት ዓመት | | የተፈቀደ በጀት | ስራ ላይ የዋለ በጀት | ሥራ ላይ የዋለው በጀት በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| 2008 | መደበኛ በጀት | 77,302,420.00 | 65,304,733.91 | 84.5% |
| | ካፒታል በጀት | 43,654,770.00 | 7,894,210.00 | 18.1% |
| | ድምር | 120,957,190.00 | 73,198,943.91 | 60.5% |
| 2009 | መደበኛ በጀት | 97,497,804.44 | 99,108,088.79 | 101.6% |
| | ካፒታል በጀት | 13,630,000.00 | 7,495,516.03 | 55 % |
| | ድምር | 111,112,804.44 | 106,603,604.82 | 95.9% |
| 2010 | መደበኛ በጀት | 102,271,920.00 | 86,466,718.87 | 84.5% |
| | ካፒታል በጀት | 28,004,700.00 | 969,552.93 | 3.46% |
| | ድምር | 130,276,620.00 | 87,436,271.80 | 67.11% |

## የኦዲቱ ዓላማ

11. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ በንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የውጪ ንግድ አፈፃፀሙን ውጤታማነት መገምገም ሲሆን፣ በዚህ ዙሪያ የሚታዩትን ችግሮችን በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦች ለማቅረብ ነው፡፡

## ለኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Audit Area)

12. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area)፤

"የወጪ ንግድ አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም"
የሚል ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues)

13. ከላይ ለተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Audit area) ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) እና ሁለት ንዑስ የትኩረት አቅጣጫዎች (sub issues) ተዘጋጅተዋል፡፡ እነርሱም፡-

1. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድን ለማሳደግ ፤ባለድረሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ እቅድ አዘጋጅቶ ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን መገምገም፤
   1.1. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በወጪ ንግድ ላይ ለሚሳተፉ አካላት ድጋፍ፤ ክትትል እና የጥራት ቁጥጥር የሚያደርግበት ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፤
   1.2.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ህገ-ወጥ የወጪ ንግድን የሚከታተልበት እና የሚቆጣጠርበት ስርአት የዘረጋ መሆኑን መገምገም፤
2. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ መረጃ አያያዝ እና አሰረጫጨት በተመለከተ ስርዓት መኖሩን እና ተግባራዊ መደረጉን መገምግም፤ የሚሉ ናቸው፡፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria)

14. በኦዲት ቡድኑ የተመረጡትን ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች እና ሁለት ንኡስ የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ 28 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የተዘጋጁትም መመዘኛ መስፈርቶች ለሚኒስቴሩ ተልከው አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹ **በአባሪ 3 ተያይዟል፡፡**

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

15. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ማንዋል (Ethiopian Performance Audit Manual) እና ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ነው፡፡ የኦዲት ሽፋኑ ከ2008 እስከ 2010 ያለውን የሦስት በጀት ዓመት አፈጻጸም ነው፡፡ ለክዋኔ ኦዲቱ በተመረጡት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች መሠረት መረጃዎቹ ተተንትነዋል፡፡ እንዲሁም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር ቃለ መጠይቅ ተደርጓል፡፡

16. ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በኢትዮጲያ ሲሆን ዋና ባለድሻ አካላት የኢትዩጲያ የንግድ እና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት፤ የኢትዮጵያ ጥራጥሬ፤ቅባት እህሎች እና ቅመማቅመም አዘጋጅቶ ላኪዎች ማህበር (EPOASPEA)፤ የኢትዮጵያ ሆልቲካልቸር አዘጋጅቶ ላኪዎች ማህበር (EHPEA)፤ እንዲሁም በናሙና ተመርጠው የታዩት 16 ላኪዎች በአካል በመገኘት ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ ከወጪ ንግድ ጋር ተያያዥነት ላያቸውን መረጃዎች ጠይቆ በመከለስ ነው፡፡(የታዩት ላኪዎች እና ማህበራት ዝርዝር በአባሪ 4 ተያይዘዋል)

# ክፍል ሁለት

# የኦዲት ግኝቶች

## 2.1. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድን ለማሳደግ ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ እቅድ አዘጋጅቶ ተግባራዊ እያደረገ ስለመሆኑ፤

**የውጪ ገበያ መዳረሻዎችን ለመለየት የሚያስችሉ ጥናቶች መጠናታቸውን በተመለከተ፤**

17. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የውጪ ገበያ መዳረሻዎችን ለመለየት የሚያስችሉ ጥናቶች ሊያካሄድ ይገባል፡፡

18. ይሁን እንጂ ነባር የገበያ መዳረሻዎችን በማስፋትና አዳዲስ ገበያዎችን ሰብሮ በመግባት የወጪ ንግድ አፈፃፀምን ለማሳደግ የሚያስችል የገበያ ጥናት በዕቅዱ መሰረት አለመከናወኑ፤ በ2008 በጀት ዓመት በሶስት አገራት በቻይና፣ ሱዳን እና ህንድ የሰሊጥ ኤግዚብሽኖችና ኮንፈረሶችን ማስተባበርና እንደ አስፈላጊነቱ መሳተፍ በሚል የተያዘው እቅድ በህንድ እና በሱዳን ያልተከናወነ መሆኑን (3 ታቅዶ 1 መፈፀሙን)፤ በ2009 በጀት ዓመት በሰሊጥ የወጪ ምርት ላይ የገበያ ጥናት ማካሄድ እና በሦስት አገራት የገበያ ቅኝት ለማካሄድ የተያዘው የሥራ ዕቅድ ያልተከናወነ መሆኑን እንዲሁም በ2010 በጀት ዓመት በቻይና እና ህንድ ዓለም አቀፍ የሰሊጥ ኮንፈረንሶች ላይ ሰሊጥ ላኪዎች እንዲሳተፉ በማስተባበር የገበያ ትስስር ለመፍጠር የተያዘው እቅድ 2 ታቅዶ 1 መሰራቱን፤በ2009 በጀት አመት የሀገሪቱን የውጪ ምርቶችን ማሳያ በአራት ቦታ በአገር ውስጥና በውጪ አገር ለመስራት የተያዘው እቅድ ያልተሰራ መሆኑን እና የወጪ ምርቶች የተወሰኑ እና በተወሰኑ የገበያ መዳረሻዎች ላይ ብቻ ጥገኛ መሆናቸውን በኦዲት ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

19. በዚህ ጉዳይ ላይ በናሙና ተመርጠው የታዩ ላኪዎች እና ሁለት የላኪዎች ማህበራት ለቀረበላቸው መጠይቅ በሰጡት ምላሽ የውጪ ገበያ መዳረሻዎችን ለመለየት የሚያስችል ጥናት ተጠንቶ እንዳልተላከላቸው እና በራሳቸው የገበያ መዳረሻዎችን የሚያፈላልጉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

20. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ጀነራል በማጠቃለያ ጥያቄ ላይ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የወጪ ንግድ ገበያ

መዳረሻዎችን ለመለየት የሚያስችል ጥናት የሌለ መሆኑን፣ ነገር ግን አንዳንድ ከውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር (ከኢምባሲዎች) ጋር የተጠኑ ጥናቶች An Internatinal Trade Center (ITC) Series on Non-Tariff Measures፡ National Green Export Review of Ethiopia Leather and Sesame Seeds Final Report ያሉ መሆኑን፣ የወጪ ምርቶች ሲላኩ በጥራት ላይ የተደገፈ ሆኖ መዳረሻዎችን በማጣራት ሊሆን ይገባል በማለት ገልፀዋል፡፡

21. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ የገበያ መዳረሻ ጥናቶች ተደርገዋል፣ በቂ ግን ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ በአገር ደረጃ ከ135 አገራት በላይ የአገራችን ምርቶች ኤክስፖርት ተደርገዋል፡፡ አንዳንድ ምርቶች በተወሰኑ ገበያዎች የበለጠ ስለሚቀርቡ የገበያ አድማሳቸውን ለማስፋት ተከታታይ ጥረት ይጠይቃል፡፡ ዕቅዶች በአቅም ማነስ፣ በመታጠፍ እና በበጀት ባለመደገፋቸው በተሟላ ሁኔታ ሳይፈጸሙ ቀርተዋል በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡በተጨማሪም ለረቂቅ ሪፖርት በተሰጠ ምላሽ በተወሰነ ደረጃ ጥናቶች ተካሂደዋል በቂ ባለመሆናቸው የበለጠ ሊሰራ ግን ይገባል በማለት ገልጸዋል፡፡

22. ነባር የገበያ መዳረሻዎችን በማስፋትና አዳዲስ ገበያዎችን ሰብሮ በመግባት የኤክስፖርት አፈፃፀምን ለማሳደግ የሚያስችል የገበያ ጥናት ባለመጠናቱ ሌሎች ያልተዳሰሱ አገራት በገበያ ለመሸፈንና መዳረሻዎችን ለማስፋት እንዳይቻል ከማድረጉም በላይ በላኪዎች በኩል ተወዳዳሪ አገራትን እንዳያውቁ በማድረግ ገበያው በሌሎች አገራት የሚወሰድበት ሁኔታ እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡

**አመታዊ የወጪ ንግድ እቅድ ሲዘጋጅ በወጭ ንግድ ላይ ባለድርሻ የሆኑ አካላትን ያሳተፈ መሆኑን በተመለከተ፤**

23. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አመታዊ የወጪ ንግድ እቅድ ሲያዘጋጅ በውጭ ንግድ ላይ ባለድርሻ የሆኑ የተለያዩ የመንግስትና የግል ባለድርሻ አካላትን ሊያሳትፍ ይገባል፡፡

24. ይሁን እንጂ የተሻለ አፈፃፀም ካላቸው እና ቢዝነስ ፕላን ከሚሞሉ ላኪዎች ወጪ ሌሎች ላኪዎችን የማያሳትፍ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

25. በዚህ ጉዳይ ላይ ለኢትዮጵያ የንግድ እና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ቃለ መጠይቅ ቀርቦላቸው በሰጡት ምላሽ፣ በየደረጃው ከምርት አቅራቢው ጀምሮ እቅድ የሌለ እና ተሳታፊ ያላደረገ መሆኑን፣ በኤክስፖርት እቅድ ሁሉንም የግል ሴክተሮች የሚያሳትፍ እቅድ አለመኖሩን፣ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ገለጸዋል፡፡

26. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ጄነራል በዳሰሳ እና ቅኝት ጥያቄ ላይ ተጠይቀው አመታዊ የወጪ ንግድ እቅድ እንደሚያዘጋጁና የእቅድ አፈፃፀሙን ለጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ ተልኮ በሚመለከታቸው የተቋቋሙ አካላት እንደሚገመገም ነገርግን አመታዊ የወጪ ንግድ እቅዱ ሲዘጋጅ ከማን ጋር እና ማንን እንደሚያሳትፍ የሚገልፅ መረጃ አለመኖሩን፣ ሁሉንም ላኪዎች ማሳተፍ እንደማይቻል ሆኖም ግን ሴክተሮችን በተናጥል የሚያሳተፉበት ሁኔታ ያለ መሆኑን፣ እንደ ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የታቀደውን እቅድ አደራጅቶ ግብርና ሚኒስቴርን፣ ቡናና ሻይ ባለስልጣንን እና ሌሎች ተቋማትን በማሳተፍ ያደረጉትን ተሳትፎ ለላኪዎች የሚልክበት ሁኔታ ያለ ቢሆንም ለሁሉም ላኪዎች አለመሆኑን፣ተሳታፊዎች በአፈፃፀማቸው እንደሚመረጡ እና ሌሎችንም ፈቃዳቸውን በመጠየቅ የሚያሳትፉበት ሁኔታ ያለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

27. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ  የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ ዓመታዊ ዕቅድ ሲዘጋጅ በተመረጡ ምርቶች ላኪ ኩባንያዎች ቢዝነስ ፕላናቸውን እንዲያቀርቡ እየተደረገ የዕቅዱ አካል ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም ዕቅዱ ከመጽደቁ በፊት ለሚመለከታቸው ሁሉ ለውይይት ቀርቦ እንዲተች ይደረጋል፡፡በአስተያየታቸውም  መሠረት  ተስተካክሎ  ወደ  ተግባር  ይገባል፡፡ የኢትዮጵያ የንግድ እና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤትም የውይይቱ አካል ነው፡፡ የአቅርቦት ዕቅድን ለማሳካት ክልሎች መነሻ ዕቅድ እንዲልኩ ከመደረጉም በላይ በውይይቱም ላይ እንዲሳተፉ ይደረጋል፡፡ የአገራዊ ዕቅድ መነሻ የሚመለከታቸው ሴክተር መ/ቤቶች (ንግድ፣ ኢንዱስትሪ፣ ግብርናና ማዕድን) ናቸው በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

28. በተጨማሪም በረቂቅ ሪፖርት ላይ በተሰጠ ምላሽ አመታዊ የወጪ ንግድ እቅድ ሲዘጋጅ የተሻለ አፈፃፀም ካላቸው እና ቢዝነስ ፕላን ከሚሞሉ ላኪዎች በስተቀር ሌሎች ላኪዎችን የማያሳትፍ ስለመሆኑ ትክክል ነው፡፡  በአሰራር ሁሉንም ላኪዎች ማሳተፍ አይቻልም አይገባምም፡፡ ሆኖም በሚደረጉ የግምገማ መድረኮች በሁሉም ላኪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው በሚመጡት ላኪዎች አማካኝነት የወጪ ንግድ እቅዱ ቀርቦ ግብአት ይሰበሰብበታል፡፡በግምገማ መድረኩ ሁሉም የግብይት ተዋንያን ባለድርሻ አካላት እንዲሳተፉ ይደረጋል በማለት ገልፀዋል፡፡

29. የመ/ቤቱ ኃላፊዎቹ ይህንን የገለፁ ቢሆንም በናሙና ካነጋገርናቸው ላኪዎች አዳዲስ ላኪዎች፣ ቢዝነስ ፕላን የማይሞሉ ላኪዎች እና በማህበር ያልታቀፉ ላኪዎች እንደማይሳተፉ የገለፁ በመሆኑ እና በውይይቱ ላይ መሳተፋቸውን የሚገልፅ ማስረጃ ባለመቅረቡ ዕቅዱ ከመጽደቁ በፊት የሚመለከታቸውን ሁሉ ያሳትፋል የሚለውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

30. የወጪ ንግድ እቅድ ላይ የሚመለከታቸው ላኪዎች እና የግል ሴክተሮች ባለመሳተፋቸው የወጪ ምርት ዕቅድን የራሳቸው አድርገው ለዕቅዱ መሳካት የራሳቸውን አስተዋጽኦ እንዳያደርጉ በማድረግ በእቅዱ መሰረት የወጪ ንግድን ኢላማ ማሳካትን አዳጋች ያደርገዋል፡፡

**ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶችን በአይነትና በመጠን የሚያድጉበት ሥርዓት መኖሩን በተመለከተ፣**

31. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶችን በአይነትና በመጠን የሚያድግበትን ሥርዓት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

32. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ምርቶችን በአይነትና በመጠን ለማሳደግ የዘረጋው ስርዓት የሌለ መሆኑን ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡


33. ምርቶች በመጠን እንዲያድጉና እንዲስፋፉ የሚያደርግ ድጋፍና ክትትል የሌለ መሆኑን፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ ላይ የሚፈለጉ ምርቶችን ለይቶ በጊዜው ለላኪው የሚያሳውቅበት እና አብሮ የሚሰራበት ሁኔታ የሌለ መሆኑን በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው መጠይቅ የቀረበላቸው ላኪዎች ገልፀዋል፡፡

34. የአገሪቱ የወጪ ንግድ እንቅስቃሴ እድገት ውስን የሆኑ የግብርና ምርቶችን መሰረት ያደረገ መሆኑን፣ የወጪ ምርቶችን በአይነትና በብዛት ለአለም ገበያ በማቅረብ የውጭ ምንዛሪ ግኝትን በሚፈለገው ደረጃ ማሳደግ አለመቻሉን፣ የግብርና ምርቶች ዋጋ መቀዛቀዝና ተወዳዳሪ መሆን አለመቻል፣ ወደ ውጭ የሚላኩ የግብርና ምርቶችን አቅርቦት በጥራት እና በመጠን ያለማደግ፣ በየዓመቱ የሚቀርበው የወጪ ምርቶች የአቅርቦት መጠንና ጥራት ወጥነት የሌለው መሆኑን፣ ምርቶችን በአይነትና በመጠን ለማሳደግ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት አለመስራቱን፣ወደ ውጭ የሚላኩ የግብርና ምርቶች እሴት ያልተጨመረባቸው መሆናቸውን፣ የኤክስፖርት ምርቶች ግብይት እና አቅርቦት የተቀላጠፈ አለመሆን እና ወደ ዘመናዊ ግብይት

ሥርዓት (ኢትዮጲያ ምርት ገበያ ድርጅት)ያልገቡ ምርቶች የኤክስፖርት ድርሻ በሚፈለገው ደረጃ ማሳደግ አለመቻሉን፣

35. እንዲሁም በ2008 በጀት ዓመት ከግብርና ምርቶች፣ ከማኑፋክቸሪንግ፣ ከማዕድን እና ከሌሎች ዘርፎች 2.753 ቢሊየን፣869.9፣600 እና 329 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማድረግ ታቅዶ፤ 2.154 ቢሊየን፣344.48፣310.54 እና 46.71 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር በቅደም ተከተል ገቢ መገኘቱ፣በበጀት ዓመቱ በድምሩ 4.22 ቢሊየን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 2.86 ቢሊየን የአሜሪካን ዶላር ገቢ መገኘቱ አፈጻጸሙ በመቶኛ 68 % መሆኑን፤በ2009 በጀት ዓመት ከግብርና ምርቶች፣ ከማኑፋክቸሪንግ፣ ከማዕድንእና ከሌሎች ዘርፎች 3.04 ቢሊየን፤ 916.84፤18.62 እና 80.60 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማድረግ ታቅዶ፤ 2.181 ቢሊየን፣ 412.93፣ 230.79 እና 82.586 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር በቅደም ተከተል ገቢ መገኘቱ፣ በበጀት ዓመቱ በድምሩ **4.75** ቢሊየን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 2.91 ቢሊየን የአሜሪካን ዶላር ገቢ መገኘቱ አፈጻጸሙ በመቶኛ 61 % መሆኑ፤

በ2010 በጀት ዓመት ከግብርና ምርቶች፣ ከማኑፋክቸሪንግ፣ ከማዕድን እና ከሌሎች ዘርፎች 3.34 ቢሊየን፤ 998.02፤ 808.604 እና 84.580 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማድረግ ታቅዶ፤ 2.16 ቢሊየን፣ 458.646፣ 120.837 እና 87.245 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር በቅደም ተከተል ገቢ መገኘቱ፣ በበጀት ዓመቱ በድምሩ **5.23** ቢሊየን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 2.83 ቢሊየን የአሜሪካን ዶላር ገቢ መገኘቱ አፈጻጸሙ በመቶኛ 54 % መሆኑን ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የእቅድ አፈፃፀም እና ከብሄራዊ ባንክ አመታዊ ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡




ግራፍ 1 ከ2008-2010 በጀት አመት የወጪ ንግድ እቅድ እና ክንውን በዶላር

36. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ጀነራል በማጠቃለያ ጥያቄ ላይ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶችን በአይነትና በመጠን የሚያድጉበት ሥርዓት ብቻውን መ/ቤቱ የሚዘረጋው ስርዓት እንዳልሆነ ነገርግን ከሌሎች ጋር በመሆን ሊሰራ እንደሚገባ ይህ ስራ በሰነድ ተደግፎና በግልፅ ተቀምጦ ማን ሊተገብረው እንደሚገባ መመሪያ ሊኖረው

እንደሚገባ ገልፀው ንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሚጠበቅበትን ስራ እንደሀገር በተቀናጀ መልኩ አለመስራቱ ሊታይ እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡

37. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው ከቻይና፣ ከኢንዶኔዥያና ከቱርክ ኢምባሲዎች ጋር በመሆን በአገራቱ በሚፈለጉ ምርቶች፣ ማሟላት ስለሚገባቸው ስፔሲፊኬሽኖች ለተመረጡ ላኪዎች ገለጻ ተደርጓል፡፡ ችግር የነበረው ላኪ ኩባንዎቹ በቦታ አለመገኘት ነው፡፡ ከግብርና ምርቶች ወደ እሴት የተጨመረባቸው ምርቶች ለመሸጋገር በኢንዱስትሪው ስትራቴጂና እርምጃዎች መሠረት የኢንዱስትሪ ፓርኮችንን ማስፋፋት፣ የአግሮ ፕሮሰሲንግ ፓርኮችን የማቋቋም እንዲሁም ኢንቨስትመንትን የማስፋፋት ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛል፡፡ ይህንኑ ጥረት በማጠናከር በሂደት የሚገጥመንን ተግዳሮቶች በጋራ በመፍታት መረባረብ ይገባናል፡፡ ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ ለመስራት የተለያዩ የውይይት መድረኮች እየተከናወኑ ይገኛል፡፡ መደረኮቹን ቀጣይነት ባለው መልኩ ማከናወን ግን ይገባል፡፡ የኢትዮጲያ ምርት ገበያ የሚገቡ ምርቶች በሂደት መበራከት ይገባቸዋል፡፡ ሆኖም የማስፋት ሥራው ከፍተኛ አቅም በሁሉም ዘርፍ የሚጠይቅ በመሆኑ አቅም በፈቀደ በአለፉት ዓመታት ሦስት ምርቶች እንዲገቡ ተደርጓል፡፤ የወጪ ንግድ አፈፃፀማችን በተጠቀሰው ደረጃ ይገኛል፡፡ ችግሩ ከአቅርቦት፣ ከሎጂስቲክስ፣ ከማስፋፊያና ትስስር፣ ከኢንቨስትመንት፣ ከግብይት ተዋንያን አቅምና አመለካከት፣ ከመፈጸምና ማስፈጸም አቅም ክፍተት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ ስለሆነም የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ቅንጅታዊ አሠራር ማዳበር ይገባናል በማለት በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አስተያየታቸውን ገልፀዋል፡፡

38. በተጨማሪም በረቂቅ ሪፖርት ምላሽ ላይ የወጪ ምርቶችን በዓይነትና በመጠን ለማሳደግ የተዘረጋ ስርዓት የሌለ መሆኑ የሚለው ስህተት ነው፡፡ ምክንያቱም እንደ ሀገር ስርዓት ተዘርግቶ በዋናነት በማኑፋክቸሪንግ ምርቶች ቅድሚያ ትኩረት እንደሚደረግ እና በተጓዳኝ ለግብርና እና የማዕድን ምርቶቻችንን የወጪ ንግዱን እንዲደግፉ እየተሰራ ይገኛል በማለት ገልጸዋል፡፡

39. የመ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዘረጋውን የአሰራር ስርዓት እና የተሰሩ ስራዎችን የሚገልጹ ማስረጃዎች ያልቀረቡ በመሆናቸው የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

40. የወጪ ምርቶችን በአይነትና በብዛት ለአለም ገበያ ማቅረብ ባለመቻሉ የውጭ ምንዛሪ ግኝትን በሚፈለገው ደረጃ እንዳያድግ እና እቅድ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ እንዲሆን አድርጓል፡፡

**በወጪ ንግድ ዙሪያ በላኪ እና ገዥ ድርጅቶች መካከል የሚፈፀሙ ኮንትራቶች ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል መመሪያ በማውጣት አፀድቆ ተግባራዊ ማድረግን በተመለከተ፤**

41. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በወጪ ንግድ ዙሪያ በላኪ እና ገዢ ድርጅቶች መካከል የሚፈፀሙ ኮንትራቶች ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል መመሪያ በማውጣት አፀድቆ ተግበራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

42. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ምርት ተልኮላቸው ለመረከብ ፍቃደኛ ያልሆኑ ተቀባዮች ላይ እርምጃ መወሰዱን የሚያረጋግጥበት የአሰራር ስርዓት የሌለ መሆኑን፤ በላኪ እና ገዥ ድርጅቶች መካከል የሚፈፀሙ የሽያጭ ውሎች ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል መመሪያ ያላወጣ መሆኑን፤ ውል የሚያፈርሱ የገዥዎች ሀገራትን በመረጃ ለይቶ ለላኪዎች እንዲጠነቀቁ የማይላክላቸው መሆኑን፤ገዥው ውል ሲያቋርጥ የሚወሰድበት እርምጃ የሌለ መሆኑን፤በላኪውና በገዥው መካካል የሚፈፀሙ ውሎች ወጥ ያለመሆናቸው፤ ሥራውን የሚደግፍ የህግ ማዕቀፍ ባለመኖሩ በውል አፈፃፀም ችግሮች ላይ ከማግባባት ባለፈ እርምጃ በመውሰድ አጥፊዎችን ለማስተማር አለመቻሉን፣ውልን አለማክበር (default) መኖርና በዚህም ምክንያት አንዳንድ የውጪ ሀገር ደንበኞች በሀገራችን ላኪዎች ላይ እምነት ማጣታቸው፣ ለማሳያ በ2009 ዓ/ም ሪክሶስ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማ የተባለ ድርጅት Hamatsing International ለተባለ የሲንጋፖር ድርጅት 6 ሙሉ ኮንቴነር የኑግ ምርት ለማቅረብ ውል የገባ ቢሆንም በውሉ መሰረት ምርቱን ባለማቅረቡ የውል መፍረስ መግጠሙ፤ ኤልያስ ሙላት ላኪ የተባለ ድርጅት ለሀጁታ ትሬዲንግ(የሀገር ውስጥ ተወካይ) ህንድ 72 ሜ.ቶን የማሾ ምርት ለማቅረብ ውል የገባ ቢሆንም በውሉ መሰረት ምርት ያላቀረበ መሆኑ፤ በ2008 ዓ/ም ጉና የንግድ ስራዎች ኃ/የተ/የግል/ማህበር ለBG HONGKONG INTERNATIONAL TRADE CO,LIMITED 190 ሜ.ቶን የሰሊጥ ምርት ለማቅረብ ውል የገባ ቢሆንም በውሉ መሰረት ምርት ያለማቅረብ ችግር ያጋጠመ መሆኑ፤ኮማ አስመጪና ላኪ ለChina SDIC International trade co.LTD 190 ሜ.ቶን የሁመራ ሰሊጥ ለማቅረብ ውል የገባ ቢሆንም ገዢው በስምምነቱ መሰረት Leter of criedt

(LC) ሊከፍት ባለመቻሉ ውሉ መፍረሱ፤በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

43. በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው የታዩት ሁለት ማህበራት እና አስራ ስድስት ላኪዎች መመሪያ እንደሌለ መመሪያው ባለመኖሩ ገዥዎች የኮንትራት ውል ሲያፈርሱ የሚገደዱበት ሁኔታ የሌለ መሆኑን፤ እንዲሁም ለኤክስፖርት አፈፃፀም ዝቅተኛ መሆን ዋነኛ ምክንያት መሆኑን ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ገለጸዋል፡፡

44. የኢትዮጲያ የንግድ እና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ውል መፍረስ ሲገጥም ገዥው የሚጠየቅበት መመሪያ (ስርአት) የሌለ መሆኑን፤ ነገር ግን የውል መፍረስ ማንዋል፤መመሪያ እና ደንብ እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል፡፡

45. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ጄነራል በማጠቃለያ ጥያቄ ላይ ተጠይቀው የውል አፈፃፀም ችግር የሀገር ገፅታ የሚያጠፋ በመሆኑ ይህን ለማስተዳደር መመሪያ የሚያስፈልግ መሆኑን፤ ነገር ግን ከውይይት በዘለለ የኮንትራት ውል መፍረስ ችግር የሚፈታበት መመሪያ የሌለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

46. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከገዥም ሆነ ከተቀባይ የሚከሰቱ የኮንትራት አለመፈጸም ችግርን ለመፍታት ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡ ላኪው ድርጅት ችግር ከፈጠረ የማማከር፣ የማገናኘትና እንዲወያዩ የማስቻል፣ በውይይቱ መሠረት ካልፈጸመ በጥቁር መዝገብ የመያዝና የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ የመጻፍ እርምጃ ይወሰዳል፡፡ በተቀባይ በኩል ተመሳሳይ ችግር ከተከሰተ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ሚሲዮኖች እንዲከታተሉት ይደረጋል፡፡ሆኖም ችግሩን በተሟላ ሁኔታ መፍታት አልተቻለም በማለት በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አስተያታቸውን ገልፀዋል፡፡

47. በተጨማሪም ለረቂቅ ሪፖርቱ በሰጡት ምላሽ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ምርት ተልኮላቸው ለመረከብ ፍቃደኛ ያልሆኑ ተቀባዮች ላይ እርምጃ መውሰዱን የሚያረጋግጥበት የአሰራር ስርዓት የሌለው መሆኑ የሚለው ስህተት ነው፡፡በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አማካኝነት ከሚሲዮኖች ጋር በመተሳሰር ችግሩ በተፈጠረበት ሀገር የሚፈታበት

ሥርዓት አለ፡፡ሆኖም ውጤታማነቱ ግን የሚጠበቀውን ያህል ላይሆን ይችላል በማለት ገልፀዋል፡፡

48. ኃላፊዎቹ ይህን ቢሉም የሽያጪ ውል መፍረስ ችግር ከመፈጠሩ በፊትም ሆነ ከተፈጠረ በኋላ ጉዳዩን ለመፍታት የሚያስችል የተዘረጋ የአሰራር ስርዓትን የሚገልፅ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

49. የውል መፍረስ ችግር የሚፈታበት ስርዓት ባለመኖሩ ገዥዎች አብዛኛውን ጊዜ ውል የሚያቋርጡ በመሆናቸው በዚህ ምክንያት የላኪዎች የመደራደር አቅማቸው እንዲቀንስ አድርጓል፡፡

**ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ ስምምነቶችን የሚፈራረምበት እና የሚያስፈፅምበት ስርአት መኖሩን በተመለከተ፤**

50. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ ስምምነቶችን የሚፈራረምበት እና የሚያስፈፅምበት ስርአት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

51. ይሁን እንጂ ለኢትዮጲያ የንግድ እና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በዚህ ጉዳይ ላይ ቃለ መጠይቅ ቀርቦላቸው በሰጡት ምላሽ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአለም አቀፍ የንግድ ስምምነቶች ሲፈራረም የግል ሴክተሩን ተሳታፊ ያላደረገ መሆኑን፤ እንዲሁም የተፈራረማቸውን ስምምነቶች በተመለከተ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የገበያ መዳረሻዎቹንና ስምምነቶችን በተመለከተ የማያሳውቅ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

52. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የንግድ ግንኙነትና ድርድር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በማጠቃለያ ጥያቄ ላይ ተጠይቀው ማህበራቱንና የንግድ ዘርፍ ምክር ቤት እናሳትፋለን እንጂ ሁሉንም ላኪዎች በተናጠል አናሳትፍም ለላኪዎችም በማህበሩ እና በምክር ቤቱ በኩል ይደርሳቸዋል በማለት ገልጸዋል፡፡

53. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው የግሉ ዘርፍ በአለም ንግድ ድርጅትም ሆነ በአፍሪካ ነጻ ንግድ ቀጠና ስምምነት በቴክኒክ ኮሚቴ አባልነት ተካቶ እንዲሳተፍ የሚደረግ ሲሆን ይህም በሚኒስትሮች ምክር ቤት መመሪያ ቁጥር 011/2009 የተካተተ ነው፡፡በተጨማሪም ከግል ዘርፉ ጋር በጋራ በስምምነቶች ዙሪያ በመሆን ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫዎች ተካሂደዋል በማለት የገለፁ ቢሆንም አንዳንድ የማህበር አባል ያልሆኑ ላኪዎች ለምሳሌ ያለሙ አስመጪና ላኪ፤ ፀሀይ ሀዱሽ የቅመማ ቅመም ላኪ እንዲሁም በለስ አስመጪ እና ላኪ የተፈጥሮ እጣን እና ሙጫ ላኪዎች ማህበር ባለመኖሩ ያልተሳተፉ መሆኑን

በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ የገለፁ በመሆኑ እና ይሳተፋሉ ለተባሉ አካላትም ማስረጃ ባለመቅረቡ ምላሹን ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

54. ላኪዎች ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተፈራረማቸው ስምምነቶች ላይ ባለመሳተፋቸው ገበያ ከማፈላለግ እና ምረቶችን ወደ ውጭ ከመላክ አንፃር ተጽእኖ ይፈጥራል፡፡

**የወጪ ንግድ በላቀ ደረጃ ለማስፋፋት የሌሎች ሀገሮችን ልምድ ለመቅሰም የሚያስችሉ ጥናቶች መኖራቸውን በተመለከተ፤**

55. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ በላቀ ደረጃ ለማስፋፋት የሌሎች ሀገሮችን ልምድ ለመቅሰም ጥናቶች ሊያከናውን ይገባል፡፡

56. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድን ለማስፋፋት የሌሎች ሀገሮችን ልምድ ለመቅሰም የሚያስችሉ ጥናቶች በማጥናት ለላኪዎች ያላከ መሆኑን በናሙና ያነጋገርናቸው ላኪዎች ገልፀዋል፡፡

57. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ጄነራል በማጠቃለያ ጥያቄ ላይ ተጠይቀው በደቡብ ኮሪያና በማሌዢያ የተሞክሮ ጥናት የተጠና ቢሆንም ለላኪዎች ግን ልምድ ለመቅሰም ተብሎ የተጠና ጥናት እና ለላኪዎች ተደራሽ የተደረገ ጥናት አለመኖሩን እና ወደፊት በስፋት የሚሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

58. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በተለያዩ ወቅት የተደረጉ ጥናቶች ለዘርፍ ማህበራት እንዲደርሱ ተደርጓል፡፡ ለወደፊት በስፋት ሊሠራበት ይገባል በማለት በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አስተያየታቸውን የገለፁ ቢሆንም ተጠንተው ለማህበራቱ ተላኩ የተባሉትን ጥናቶች ማስረጃ ያልቀረቡ በመሆናቸው አስተያየቱን ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

59. በመሆኑም ላኪዎች የገበያ መዳረሻዎችን እንዳያሰፉ፤ አዳዲስ ደንበኞች እንዳያገኙ የኤክስፖርት ስራ እንዳይሰፋ ፤ በዋጋ ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ፤ ከሌሎች አለም ገበያ አንፃር ያለውን የኤክስፖርት ችግር በማየት አሻሽሎ ለመስራት እንዳይቻል ምክንያት ሆኗል፡፡

**ለወጪ ንግድ ማነቆ የሆኑ ችግሮች ጥናት በማከናወን የተለዩ መሆናቸውን በተመለከተ፤**

60. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለወጪ ንግድ ማነቆ የሆኑ ችግሮች ጥናት በማከናወን ሊለይ እና የመፍቻ ስርአት ሊዘረጋ ይገባል ፡፡

61. ይሁን እንጂ የወጪ ንግድ ማነቆዎችን ለመፍታት ከሚደረገው ጥረት አኳያ፤ የወጪ ንግድ ማነቆ መስፋፋቱን፤ ግልፅ የሆነ የመፍቻ ሥርዓት አለመኖሩን፤ለኤክስፖርት የኮንትሮባንድ ንግድ፤ የማኔጅመንትና የቴክኒክ አቅም ውስንነት፣ የግብዓት አቅርቦት ውስንነት መኖሩን በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

62. በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው ጥያቄ የቀረበላቸው የተፈጥሮ ሙጫ እና እጣን ላኪዎች በሰጡት ምላሽ የተፈጥሮ ሙጫ እና እጣንን በተመለከተ የምርቱ ሁኔታ ቦታው ከፀጥታ አንፃር አስተማማኝ ያለመሆኑ፤ምርቱ የሚሰበሰብበት ደን ያለመጠበቁ፤ ችግሮች ያሉ ቢሆንም የተፈታበት ሁኔታ የሌለ መሆኑን፤ ሴክተሩ ቦታ ተሰጥቶት ጥናት ያልተደረገበት እና በስፋት ያልተሰራበት መሆኑን የገጠሟቸው ችግሮች መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

63. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ጄነራል በማጠቃለያ ጥያቄ ላይ ተጠይቀው በወጪ ንግድ ዙሪያ የሚገጥሙ ችግሮች ተለይተው የተቀመጡ ቢሆንም ችግሮቹ የሚፈቱበት ስትራቴጂ ያለመኖሩን እና በቅንጅት ለመፍታት እየተሞከረ ቢሆንም መሬት ወርደው የተፈቱ ችግሮች የሌሉ መሆኑን፤ችግሮችን ለመፍታት የተዘረጋ ሥርአት የሌለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

64. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ተፈጥሮ ሙጫንና ዕጣን በባህሪው ራቅ ያሉና መሠረተ ልማት ባልተሟላባቸው ቦታዎች የሚመረቱ ሲሆን በሂደት ከአገሪቱ የመሠረተ ልማት ማስፋፋት ስትራቴጂ የሚፈታ ጉዳይ ነው፡፡ የወጪ ንግድ ችግሮቹ ያሉ ሲሆን በቅንጅት ሊፈቱ የሚገባ ሲሆን ቅንጅታዊ አሠራሮች መዳበር ይገባቸዋል በማለት አስተያየታቸውን ገልፀዋል፡፡

65. ጥናት በማከናወን ለወጪ ንግድ ማነቆ የሆኑ ችግሮች ባለመለየታቸው እና ችግሮችን የመፍቻ ስርአት ባለመኖሩ በኤክስፖርት ዙሪያ የሚታዩ ችግሮች ደረጃ በደረጃ እንዳይፈቱ ምክንያት ሆኗል፡፡

## 2.2 ሚኒስቴር መ/ቤቱ በወጪ ንግድ ላይ ለሚሳተፉ አካላት ድጋፍ፣ክትትል እና የጥራት ቁጥጥር የሚያደርግበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ እያደረገ ስለመሆኑ፤

**የወጪ ንግድ ምርቶችን የሚልኩ ላኪዎች በአለም ገበያ በስፋት ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ድጋፍ እና ክትትል መደረጉን በተመለከተ፤**

66. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ ምርቶችን የሚልኩ ላኪዎች በአለም ገበያ በስፋት ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ድጋፍ እና ክትትል የሚያደርግበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

67. ይሁን እንጂ በናሙና ተመርጠው የታዩ ላኪዎች እና ማህበራት፤ የኢትዮጵያ ሆልቲካልቸር አዘጋጅቶ ላኪ ማህበር፣ፀሀይ ሀዱሽ ላኪ፣ያልሙ አስመጪና ላኪ፣በለስ ኃ/የተ/ የግ/ ማህበር እና ጀሚላ ባይሩ ላኪ ቢዝነስ ፕላን የማይሞሉ እና ድጋፍ እና ክትትል የማይደረግላቸው መሆኑን ሲገልፁ አንድ ማህበርና አስራ ሁለት ላኪዎች ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚላክላቸውን ቢዝነስ ፕላን ፎርም ሞልተው እንደሚልኩ ነገርግን በእቅድ ተይዞ የተደረገላቸው ድጋፉና ክትትል የሌለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

68. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሁለት ኢምባሲዎች እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ለ100 ላኪዎች በየሃገራቱ የንግድ ግንኙነት ላይ የግንዛቤ ማዳበሪያ ስልጠና ለመስጠት በ2010 በጀት አመት በዕቅድ ቢያዝም አለመተግበሩን፤ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2010 በጀት አመት በ"Market Research" እና "Market Intellegence" ላይ ስልጠና የመስጠት ዕቅድ ተይዞ ያለመተግበሩን፤በሚኒስቴር መ/ቤቱ በአምራች ክልሎች የሚደረገው የመስክ ክትትልና ድጋፍ በታቀደው መሠረት ወቅቱን ጠብቆ በተከታታይ አለመከናወኑን እና አንዳንድ የመስክ ክትትልና ድጋፍ ሥራዎችም ውጤት ያመጡ አለመሆኑን፣ ለላኪዎች ከወጪ ንግድ ጋር (ከሙያው) ጋር የተገናኘ ስልጠና ያልተሰጠ መሆኑን፤ ላኪዎችን በቢሮ ከመከታተል አልፎ በመስክ ስራ ቦታ ተገኝቶ ክትትል እና ድጋፍ ያልተደረገ መሆኑን በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

69. ለኢትዮጵያ የንግድ እና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በዚህ ጉዳይ ላይ ቃለ መጠይቅ ቀርቦላቸው በሰጡት ምላሽ፤ ድጋፍ እና ክትትል ተደርጎ ተግባራዊ የሆነበት ሁኔታ የሌለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

70. በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው መጠይቅ የተደረገላቸው ላኪዎች በሰጡት ምላሽ ድጋፍና ክትትል ያልተደረገላቸው መሆኑን፤ በኤክስፖርት ስራ ላይ የሚገጥሟቸው ችግሮች እየተፈቱ አለመሆኑን፤በተናጥል የኮንትራት ችግር ሲገጥማቸው እና መረጃ ሲፈልጉ ድጋፍ ከማድረግ ውጪ በእቅድ ተይዞ በተጠናከረ መልኩ የሚደረግላቸው ድጋፍ እና ክትትል የሌለ መሆኑን፤ የሚገባቸውን ማበረታቻ አለማግኘታቸውን፤ በላኪዎች በኩል የግብይት ዕውቀት፣ ልምድና ክህሎት ውስንነት ምክንያት የመደራደር፣የመወሰን እና ኮንትራትን የማስተዳደር አቅም ማነስ መኖሩን ገልፀዋል፡፡

71. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሰብል ምርቶች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በማጠቃለያ ጥያቄ ላይ ተጠይቀው ላኪዎች በዘርፉ እንዲሰሩ ከመስራት አንፃር ከገቢዎችና ጉምሩክ ጋር በመሆን አንዳንድ የድጋፍ ስራዎች የተደረጉበት አጋጣሚዎች ያሉ ቢሆንም እነዚህ የድጋፍና ክትትል ስራዎች በቂ እንዳልሆኑ፤ ስልጠና ያልተሰጠ መሆኑን የማበረታቻ ስርዓቱ የቀረ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

72. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ተጠይቀው የድጋፍና ክትትል ተግባር የወጪ ምርቶችን በቀጥታ እንዲከታተሉ ኃላፊነት የተሰጣቸው ሴክተር መሥሪያ ቤቶች በተናጠል የሚያከናውኑት ተግባር ነው፡፡ ኦዲቱ የሚመለከተው የቀድሞው የንግድ ሚኒስቴር ለሚከታተላቸው ሰብሎች ቢዝነስ ፕላን በማዘጋጀት የቅርብ ክትትልና ድጋፍ እያደረገ ስለመሆኑ በሪፖርቶች ተገልጸዋል፡፡ የድጋፍና ክትትል ሥራው ከዘርፍ ማህበራት ጋር በመቀናጀት የማይሰራ በመሆኑ የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ምክር ቤት በቂ መረጃ ላይኖረው ይችላል፡፡ በናሙና የተመረጡ ላኪዎች ለተባለው ቅድሚያ ትኩረት ለሚሰጣቸው ምርቶች የሚከናወን በመሆኑና ምናልባትም የናሙናው ወካይነት ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ስልጠና አቅም በፈቀደ ተሰጥቷል፡፡ አንዳንድ ስልጠናዎች በፕሮጀክት ተይዘው ፕሮጀክቱ በተራዘመ ሂደት በመፈቀዱ በተያዘው ጊዜ አልተፈጸሙም ሆኖም ዘግይተውም ቢሆን በ"Market Research" እና "Market Intellegence" ስልጠናዎች ዘንድሮ ተሰጥተዋል፡፡ በክልሎች አቅም በፈቀደ የመስክ ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡ ሆኖም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከነበረበት ከፍተኛ የትራንስፖርት መኪና ችግር አኳያ በተሟላ ላይፈጸም ችሏል በማለት ገልጸዋል፡፡

73. በተጨማሪም በረቂቅ ሪፖርት ምላሽ ላይ የወጪ ገበያውን በተገቢው ሁኔታ ባለመጠቀማችን ከአቅርቦት አነስተኛነት ባሻገር በተደራጀ ሁኔታ የወጪ ገበያውን ለመጠቀም የሚያስችል የድጋፍና ክትትል ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑን የሚለው ስህተት ነው፡፡ምክንያቱም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ቀጥታ ክትትል ለሚያደርግባቸው ምርቶች አደረጃጀት በመፍጠር የዕለት ከዕለት ክትትል እና ድጋፍ ከማድረግ ባሻገር ሀገራዊ አፈፃፀም ሪፖርት እያዘጋጀ ለሚመለከተው በማቅረብ ውይይት እንዲደረግበት እና አቅጣጫ እንዲሰጥበት እየተደረገ በመሆኑ በማለት ገልፀዋል፡፡

74. ይሁን እንጂ የቢዝነስ ፕላን ፎርም ለሚሞሉት ላኪዎች ፎርም ከማስሞላት እና ድጋፍ ሲጠይቁ ድጋፍ ከማድረግ ውጪ በእቅድ ተይዞ የተደረገላቸው ድጋፍ እና ክትትል የሌለ መሆኑን እንዲሁም ቢዝነስ ፕላን የማይሞሉ ላኪዎች ምንም አይነት ድጋፍ እና ክትትል ያልተደረገላቸው መሆኑን በናሙና ያነጋገርናቸው ላኪዎች የገለፁ በመሆኑ እና ድጋፍ እና ክትትል ለማድረግ የተላከ ደብዳቤም ሆነ ሌላ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ፤የቀድሞው የንግድ ሚኒስቴር ለሚከታተላቸው ሰብሎች ቢዝነስ ፕላን በማዘጋጀት የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል የሚለውን አስተያየት ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

75. ላኪዎች ባዘጋጁት የወጪ ንግድ እቅድ መሰረት ኮንትራት እንዲገቡ እንዲልኩ ድጋፍ እና ክትትል ባለመደረጉ ከላኪዎች በኩል የኮንትራት ውል አለማክበር እንዲኖር ምክንያት ሆኗል፡፡

**የወጪ ንግድ ለማጠናከር ከላኪዎችና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የውይይት መድረክ መኖሩን በተመለከተ፤**

76. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ ለማጠናከር ከላኪዎችና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የውይይት መድረክ ሊኖረው ይገባል፡፡

77. ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ላኪዎች የገጠማቸውን ችግር ለመፍታት የተዘጋጀ ስርዓት አለመኖሩን፣ በየሩብ ዓመቱ የሚካሄደው የላኪዎችና የባለድርሻ አካላት የጋራ ውይይት መድረክ በታቀደው መሠረት ወቅቱን ጠብቆ በተከታታይ አለመከናወኑን፣ በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት መካከል ያለው ቅንጅታዊ አሰራር የተጠናከረ አለመሆኑን፣የላኪዎችና የባለድርሻ አካላት የጋራ መድረክ ውይይት በ2008 ዓ/ም በእቅድ ተይዞ የተከናወነ ተግባር ቢሆንም በ2009 ዓ/ም እና በ2010 ዓ/ም በእቅድ

ያልተያዘና ያልተከናወነ መሆኑን በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

78. በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው መጠይቅ የተደረገላቸው ላኪዎች በማህበር ያልታቀፉ ሳሙኤል ብርሀነ (አክማስ) አስመጪና ላኪ፣ ፣ፀሀይ ሀዱሽ ላኪ ፣ ያልሙ አስመጪና ላኪ ፣በለስ ኃ/የተ/የግ/ ማህበር፣ ጀሚላ ባይሩ ላኪ ንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ባዘጋጀው መድረክ ተሳትፈው እንደማያውቁ ገልፀዋል፡፡

79. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሰብል ምርቶች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በማጠቃለያ ጥያቄ ላይ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ተጠይቀው ሁሉንም ላኪዎች የማያሳትፉ መሆኑን፤ ቢዝነስ ፕላን የሞሉትን ብቻ የሚያሳትፉ መሆኑን፤ ነገር ግን ሁሉም ቢሳተፉ የተሻለ እነደሆነ፤ እንደ ሀገር የቅንጅታዊ አሰራር ችግር ያለ መሆኑን፤ ትልቁ የኤክስፖርት ችግር ቅንጅታዊ አሰራር ችግር መሆኑን፤ ሁሉም ላኪዎች ችግሮቻቸውን በውይይት አንስተው ሙሉ በሙሉ መፍትሄ የሚያገኙበት ሁኔታ የሌለ መሆኑን፤ የኢትዮጲያ ምርት ገበያ በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ የእስታዳርድ ችግር ያለበት መሆኑን፤ ይህም በላኪዎች የሚነሳ ችግር መሆኑን ገልፀዋል፡፡

80. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ተጠይቀው በአብዛኛው የጋራ ምክክር መድረኮች ተደርገዋል፡፡ ሆኖም በአመራር መለዋወጥ ምክንያት የመድረኮች መቆራረጥ ገጥሟል፡፡ ሆኖም ባለሙያዎች በቅርብ ክትትል የማድረግ ሥራዎች መከናወናቸው በሪፖርቶች በግልጽ ተመላክቷል፡፡ በማለት በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አስተያታቸውን የገለፁ ቢሆንም በናሙና ካነጋገርናቸው ላኪዎች በማህበር ያልታቀፉ እና አዳዲስ ላኪዎች ንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ባዘጋጀው መድረክ ተሳትፈው እንደማያውቁ የገለፁ በመሆኑ እና ለውይይት ለመጋበዝ እና ክትትል ለማድረግ የተላከ ደብዳቤም ሆነ ሌላ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ አስተያየቱን ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

81. ሁሉንም ላኪዎች ያሳተፈ እቅድ ባለመኖሩ እና ላኪዎች የገጠማቸውን ችግር ለመፍታት የተዘጋጀ ስርዓት ባለመኖሩ እንዲሁም በእቅድ የሰራው የቱ ነው ከእቅድ በላይ የሰራው የቱ ነው የሚለውን የሚከታተሉበት ሁኔታ ባለመኖሩ ከፍተኛ አፈፃፀም ብለው የሚያወጡት ላኪ ያለምንም መመዘኛ መስፈርት እንዲሆን አድርጓል፡፡

ላኪዎች ባዘጋጁት የወጪ ንግድ ዕቅድ መሰረት ኮንትራት እንዲገቡ እና እንዲልኩ ክትትልና ድጋፍ መደረጉን በተመለከተ፤

82. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ላኪዎች ባዘጋጁት የወጪ ንግድ ዕቅድ መሰረት ኮንትራት እንዲገቡ እና እንዲልኩ ድጋፍ እና ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡

83. ይሁን እንጂ እንደሀገር የወጪ ገበያውን በተገቢው ሁኔታ ላለመጠቀማችን ከአቅርቦት አነስተኝነት ባሻገር በተደራጀ ሁኔታ የወጪ ገበያውን ለመጠቀም የሚያስችል የድጋፍ እና ክትትል ስርአት ያልተዘረጋ መሆኑን ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

84. በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ ላኪዎች እና ሁለት ማህበራት ውስጥ አስራ ሶስቱ ላኪዎች እና አንድ ማህበር (የኢትዮጲያ ሆልቲካልቸር አዘጋጅቶ ላኪ ማህበር) ወደ ውጭ ለመላክ ያላቸውን የምርት መጠን በስልክ ደውሎ ከመጠየቅ ውጪ የሽያጪ ውል እንዳይፈርስ ገዥዎችን ከማገናኘት አንፃር የተደረገላቸው ድጋፍና ክትትል የሌለ መሆኑን፤ላኪዎች ባዘጋጁት የወጪ ንግድ ዕቅድ መሰረት ኮንትራት እንዲገቡ እና እንዲልኩ ከሚ/መ/ቤቱ የሚደረግ ድጋፍና ክትትል የሌለ መሆኑን፤ ከጉምሩክ፣ ከመብራት እና ከሎጀስቲክ ጋር የተገናኙ ችግሮችን የማይፈታ መሆኑን፤ የመሸጫና የመላኪያ ዋጋ ተመን መረጃ የማይደርሳቸው መሆኑን፤አንዳንድ የግብርና ምረቶች ለምሳሌ የተፈጥሮ ሙጫ እና ቅመማቅመም አስገዳጅ የጥራት ደረጃ ያልወጣላቸው በመሆኑ ላኪው የሚልክበትን የጥራት ደረጃ ያለማወቅ ችግር መፍጠሩን፤ምርት ወደ ውጭ ለመላክ የሚያጋጥሟቸው ችግሮች መሆናቸውን፤በናሙና ያነጋገርናቸው ላኪዎች ገልፀዋል፡፡

85. ስለሁኔታው የሚኒስቴሩ የሰብል ምርቶች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በማጠቃለያ ጥያቄ ላይ ተጠይቀው ለሁሉም ላኪዎች ድጋፍ እና ክትትል እንደማያደርጉ፤ የተሻለ አፈፃፀም ላላቸው ብቻ ድጋፍ እና ክትትል እንደሚደረግ እሱም በቂ እንዳልሆነ፤የሚፈፀሙ ውሎች ሲመጡ የሚጠበቅባቸውን ሁኔታ ያለሟሟላት ሁኔታ ያለ መሆኑን፤ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩልም ያልተሟላውን ኮንትራት አጣርቶ የመረከብ እና የማደራጀት ችግር ያለ መሆኑን፤ቢዝነስ ፕላንም የሚሞላው በላኪው ፈቃደኝነት እንጂ ከመ/ቤቱ የሚያስገድድ ሁኔታ የሌለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

86. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ተጠይቀው በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ምርቶችን ለማስገባት ከፍተኛ የሚባል

የመሠረተ ልማት ዝግጅት ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም ምርቶች በሂደት ወደ ሥርዓቱ የሚገቡበት አሠራር መከተል ግድ ይላል፡፡ አስገዳጅ የጥራት ደረጃ ከምርቶቹ ባህሪና ኢኮኖሚዊ ጠቀሜታ እንዲሁም ከመቆጣጠር አቅም አንፃር እየተፈተሸ የሚገባ ሲሆን እንዲገቡ ፍላጎት ያለው ግለሰብም ሆነ ማህበር ጉዳዩን ለሚከታተለው አካል ማቅረብ ይችላል፡፡ በአብዛኛው ኮንትራት መፍረስ የሚገጥመው በላኪው ጥቃቅን ችግሮች ምክንያት ነው፡፡ ለአብነትም በተስማማው የጥራት ደረጃና ጊዜ አለመላክ ወይም ሰነድ በአግባቡ ባለማዘጋጀት፣ ስለሆነም የበለጠ በጋራ ልናርመው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ ሆኖም ችግሩ ሲገጥም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ሚሲዮኖች ድጋፍ እንዲያደርጉ መረጃ ይተላለፍላቸዋል በማለት አስተያየታቸውን ገልፀዋል፡፡

87. ላኪዎች ባዘጋጁት የወጪ ንግድ ዕቅድ መሰረት ኮንትራት እንዲገቡ እና እንዲልኩ ድጋፍና ክትትል ባለመደረጉ በላኪዎች በኩል ከወቅቱ የገበያ ዋጋ በታች የሽያጭ ውል መግባትና ውልን በማፍረስ (default) በሃገራችን የገበያ ገፅታ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ፈጥሯል፡፡ለማሳያ በ2008 ዓ/ም 37 ላኪዎች፣በ2009 ዓ/ም 11 ላኪዎች፣በ2010 ዓ/ም 22 ላኪዎች የቅባት እህሎች፣የጥራጥሬ እና የቅመማ ቅመም ላኪዎች የኮንትራት ውል መፍረስ (default) ገጥሟቸዋል፡፡

**ወደ ውጭ አገር የሚላኩ የሀገሪቱ ምርቶች በዓለም ገበያ ታዋቂ እንዲሆኑ መለያ የንግድ ምልክት (ብራዲንግ) እንዲኖራቸው መደረጉን በተመለከተ፣**

88. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወደ ውጭ አገር የሚላኩ የሀገሪቱ ምርቶች በዓለም ገበያ ታዋቂ እንዲሆኑ መለያ የንግድ ምልክት (ብራዲንግ) እንዲኖራቸው ሊያደርግ ይገባል፡፡

89. ይሁን እንጂ መለያ የንግድ ምልክት (ብራዲንግ) በቡና፣ በሰሊጥ፣ በጤፍ እና በማር ላይ በ2011 ዓ/ም የተጀመረ ቢሆንም በሌሎቹ የወጪ ምርቶች የሌለ መሆኑን ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

90. በአትክልት እና ፍራፍሬ ላይ ብራዲንግ የሚሰጠው እራሱ አምራቹ መሆኑን፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያደርገው የክትትል ተግባር የሌለ መሆኑን፣ በናሙና ያነጋገርናቸው ላኪዎች ገልፀዋል፡፡

91. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ጄነራል በማጠቃለያ ጥያቄ ላይ ተጠይቀው ብራንዲግ ቡና፣ጤፍ፣ ማር እና ስሊጥ

ላይ እየተሰራ መሆኑን፣ ለወደፊትም እንደአስፈላጊነቱ የሚሰራበት ሁኔታ ይኖራል በማለት ገልፀዋል፡፡

92. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው የብራንዲግ ሥራ ከፍተኛ ባለሙያ የሚጠይቅ ከተሠራም በኋላ ከፍተኛ ክትትል በማድረግ ውጤታማነቱን ማረጋገጥ የሚገባ በመሆኑ የተጀመረውን በማጠናቀቅ ውጤታማ ለማድረግ ከፍተኛ ትኩረት ማድረግ ይገባል፡፡ ያለብራንድ ኮንትራት ዝብርቅርቅ ይላል የሚለው ጉዳይ ሊታይ ይገባል፡፡ ምክንያቱም የአገሪቱን ምርቶች በሙሉ ብራንድ አድርጎ መሸጥ ስለማይቻል፡፡ ስለሆነም ኮንትራት በምርቱ አይነት በሚፈለገው የምርት ጥራት ደረጃ በመግባት ወጪ ንግድን ማራመድ ግድ ይላል፡፡ በማለት በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አስተያታቸውን ገልፀዋል፡፡

93. ወደ ውጭ አገር የሚላኩ የሀገሪቱ ምርቶች መለያ የንግድ ምልክት (ብራዲንግ) የሌላቸው በመሆኑ፣የሀገሪቱን ምርት ከሌላ አገራት ጋር ያለውን ጥራት ለመለየት እንዳይቻል ከማድረጉም በላይ የሀገራችን ምርት ወደብ ላይ በሌሎች ሀገሮች የመሰረቅ ሁኔታ እንዲኖር እንዲሁም ኮንትራት ላይ ምርቱ ዝብርቅርቅ ያለ ስም እየተሰጠው ውል እንዲገባ አንዲሁም ሌሎች ሀገራት ከኢትዮጲያ እየወሰዱ ምርቱ ላይ እሴት በመጨመር (value added) ወደ ሌላ ሀገር በመሸጥ ሀገሪቷ ማግኘት ያለባትን ተጨማሪ የውጭ ምንዛሬ እንድታጣ ምክንያት ሆኗል፡፡

**ወደ ወጪ የሚላኩ ምርቶችን ጥራታቸውን የጠበቁ ባለመሆናቸው ከገዢዎች ጋር አለመግባባት እየተፈጠረ መሆኑን በተመለከተ፣**

94. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶችን ጥራታቸውን የጠበቁ መሆናቸው የሚረጋገጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

95. ይሁን እንጂ የቅባት እህሎችና ጥራጥሬ ምርቶች በሚፈለገው መጠን እና የጥራት ደረጃ እንዲሁም በተወዳዳሪ ዋጋ መቅረብ አለመቻላቸውን፣ በአንዳንድ የግብይት ተዋንያን በኩል በበቂ መረጃ ላይ ባልተመሠረተ የገበያ ትንበያ (Speculations) ምርት በክምችት በመያዝ ጥራት የሚያጓድሉ መሆኑን፣ ምርትና ምርታማነትን እንዲሁም ጥራትን የሚያሻሽሉ ግብዓቶች እና ቴክኖሎጂዎች አለመኖራቸውን፣ የምርት ማከማቻ መጋዘኖች ዘመናዊ አለመሆናቸውን፣ ዘመናዊ የሆነ ላብራቶሪ ባለመደራጀቱ የደንበኞች መጉላላት፣ አዳዲስ ዘመናዊ አሰራርና የቁጥጥር ስርዓት

አለመዘርጋቱን፤ነባር ዘር ተጠቅመው የዘሩት ሽንብራ ለውጭ ገበያ ሲቀርብ ተገቢውን ዋጋ ለማግኘት እንዳላስቻላቸው፣ አንድ ቶን ሽንብራ እስከ 900 ዶላር መሸጥ እየተቻለ፣ ምርጥ ዘር ባለመኖሩ ሳቢያ በ450 ዶላር ለመሸጥ መገደዳቸውን በመግለጽ የምርጥ ዘር አቅርቦት እጥረት የግብርና ምርቶችን የወጪ ንግድ እየጎዱት መሆኑን፤

96. በተጨማሪም እንደ ሀገር የላብራቶሪ አቅም የሌለ በመሆኑ የጥራት ችግር መኖሩን፤ እንዲሁም የአፍላ ቶክሲንና የኬሚካል ችግሮች የሚፈተሹበት ላብራቶሪ የሌለ በመሆኑ በኢትዮጲያ የጥራት ደረጃው የተረጋገጠ ምርት በገዥው ድርጅት ሲመረመር የጥራት ጉድለት የሚታይበት መሆኑን፤ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

97. በዚህ ጉዳይ ላይ በናሙና ያነጋገርናቸው ላኪዎች የተፈጥሮ እጣን እና ሙጫ በተመለከተ በሀገር ደረጃም የወጣለት መሰፈርትና ደረጃ የሌለ በመሆኑ ጥራቱን የሚያረጋግጥበት ስርዓት የሌለ መሆኑን፤ምርቱም የሚላከው ገዥና ሻጭ በመስማማት ብቻ መሆኑን፤ላኪዎች ወደ ምርት ገበያ የገቡትን ምርቶች የምርት ደረጃዎችን በትክክለኛው በከፈሉት የጥራት ደረጃ መጠን የማያገኙ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

98. ለኢትዮጵያ የንግድ እና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በዚህ ጉዳይ ላይ ቃለ መጠይቅ ቀርቦላቸው በሰጡት ምላሽ የጥራት ቁጥጥርን በተመለከተ የተዘረጋ ስርዓት የሌለ መሆኑን፤ ይህም በአብዛኛው የኮንትራት ውል ማፍረስ በኢትዮጵያ ላኪዎች እንዲከሰት ምክንያት መሆኑን፤ ለምሳሌ አንድ የእስራኤል ካምፓኒ(ገዢ) ከኢትዮጵያ ታምሪን ከተባለ ላኪ ድርጅት 25 ኮንቴነር ሰሊጥ ለመገበያየት ውል ተገብቶ በላኪው በኩል የምረት ጥራት ችግር በመኖሩ፤ መፍትሄ እንዲሰጣቸው ለኢትዮጵያ የንግድ እና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በጠየቁት መሰረት የኢትዮጵያ የንግድ እና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ለላኪው ድርጅት ደብዳቤ የፃፈ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

99. የቅባት እህሎች ለምሳሌ ኑግ የጥራት ደረጃ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መምጣቱን፤ የምርት ጥራትና የብቃት ማረጋገጫ አለመሰጠት ችግር መኖራቸውን ለምሳሌ፡- KAFFEE PURA GmbH የተባለ የጀርመን ኩባንያ ELNATURE PROCESSED FOOD EXPORTER ከተባለ የኢትዮጲያ ድርጅት መጠኑ ያልታወቀ በርበሬ ጀርመን ሀገር ከደረሰ በኋላ ስታንዳርዱን የጠበቀ አይደለም በማለት እንዲመለስ የተደረገ

መሆኑን፤AHCOF HOLDINGS CO,LTD የተባለ የቻይና ኩባንያ በላቸዉ ጀምበሬ አስመጪና ላኪ ከሚባል ድርጅት የኢትዮጲያ (የሁመራ ሰሊጥ) በጥራት መጓደል ምክንያት ምርቱ ቻይና ወደብ ከደረሰ በኋላ ሊረከብ አለመቻሉን በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

100. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የገቢና ወጪ እቃዎች ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ዳይርክተር በማጠቃለያ ጥያቄ ላይ ተጠይቀው ሚኒስቴር መ/ቤቱ እየተቆጣጠረ ያለው አስገዳጅ ደረጃ ያላቸውን ምርቶች ብቻ መሆኑን፤ በፍቃደኝነት የሚሰጡ ደረጃዎችም መኖራቸውን፤ የተፈጥሮ ሙጫና እጣን አስገዳጅ ደረጃዎች ውስጥ ያልገቡ መሆኑን፤ በቀጣይ ግን ሁሉም ምርቶች ወደ አስገዳጅ ደረጃ ቢገቡ የተሻለ መሆኑን፤ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያጣራው የሀገሪቱን ጥራት አሟልቷል የሚለውን ቢሆንም ገዥው ድርጅት በሌላ ድርጅት በማስመርመር ሲገዛ የጥራት ችግር የሚታይበት መሆኑን፤ ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶች የአፍላ ቶክሲንና የኬሚካል ችግሮች ለመመርመር እንደ ሀገር የላብራቶሪ አቅም ስለሌለ የሚፈተሸበት ላብራቶሪ እንደሚያስፈልግ እንዲሁም ቅመማቅመምና በርበሬ ሌሎች ምርቶች ወደ ደረጃ ስላልገቡ ሊገቡ እንደሚገባ፤ኤክስፖርት ሊደረግ ሲል ናሙና በመውሰድ የሚደረግ የጥራት ፍተሻ አዋጪ እንዳልሆነ፤ከምርቱ ጀምሮ ጥራቱ ቢታይ የተሻለ መሆኑን በአጠቃላይ የጥራት ቁጥጥር ስርዓት ቢኖርም በስፋት ወደፊት ይሰራበታል በሚል ቢታይ በማለት ገልፀዋል፡፡

101. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው የተፈጥሮ እጣንና ሙጫ ደረጃ አለው፡፡ ሆኖም ወደ አስገዳጅነት ለመለወጥ ማህበሩ ፍላጎት ስላለው ከሚመለከተው የጥራት ኤጀንሲ ጋር የሚሠራበት ይሆናል፡፡ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ አገልግሎት አሠጣጥ ከጥራት ደረጃ ጋር ተያይዞ የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት ጥረት እየተደረገ በመሆኑ መሻሻሎች አሉ፡፡ ለኮንትራት ውል መፍረስ ዋነኛው ምክንያት ጥራት ሳይሆን ዋጋ ነው፡፡ ኮንትራት ሲገባ የነበረው የአገር ውስጥ ዋጋ ዝቅተኛ ሆኖ እንደተገባ ከመጨመር ጋር ተያይዞ ወይም የአለም ገበያ ዋጋ በመጨመር ምክንያት ኮንትራት ይፈርሳል፡፡ ሆኖም መንግሥት ኮንትራት መፍረስ እንደሌለበትና ችግር ሲገጥም የማወያየት እንዲሁም የማስጠንቀቂያ የመፈጸም እርምጃ እየወሰደ ይገኛል፡፡ ለወደፊትም እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል መመሪያ በማዘጋጀት ላይ ነው፡፡ ለወጪ ንግድ ጥራት መሠረታዊ መስፈርት ነው፡፡ጥራት በመሠረቱ ምርቱ ከሚመረትበት ከአርሶ አደሩ የሚጀምር ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም

ምርቱ ከተመረተበት ወደብ እስከሚደርስበት ድረስ ጥራቱ እንዳይበላሽ የተቀናጀ ጥረት ማድረግ ይገባል፡፡ለዚህም በየደረጃው በጥራት ላይ ተከታታይ ስልጠና መስጠት ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ ጅምር ጥረት ቢኖርም አጠናክሮ መቀጠል ተገቢ ነው፡፡በተጨማሪም በአብዛኛው ጥራት የሚጓደለው በግብይት ሂደት በመሆኑ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ እንዲሁም ቁጥጥር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም በየደረጃው በሁሉም አካል የጋራ ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ ጥራት እንዲቆጣጠሩ ስልጣን የተሰጣቸው ከወረዳ እስከ ክልል የሚገኙ አካላት የጥራት ሁለገብ ሥራቸውን ማጠናከር ይገባቸዋል በማለት በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አስተያየታቸውን ገልፀዋል፡፡

102. በረቂቅ ሪፖርት ምላሽ ላይ የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች በሚፈለገው መጠን እና ጥራት ደረጃ እንዲሁም በተወዳዳሪ ዋጋ መቅረብ ያለመቻላቸው ትክክል ነው፡፡ሆኖም ይህን የማድረግ ኃላፊነት በዋናነት የሚመለከተው አካል ያለ በመሆኑ በየጊዜው ችግሩን በማሳወቅ ረገድ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡የሚመለከተው አካልም ለስራው ትኩረት በመስጠት እየተንቀሳቀሰ ይገኛል በማለት ገልጸዋል፡፡

103. ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶች ጥራት መጓደል (የወጪ ምርቶች ጥራት አጠባበቅና ቁጥጥር ደካማ መሆን) ገዥዎች የኮንትራት ውል እንዲያፈርሱ ምክንያት ከመሆኑም በላይ የምርቱን ተወዳዳሪነትና የሚያስገኘውን የውጭ ምንዛሬ ገቢ ለማሳጣት ምክንያት ሆኗል፡፡

**የወጪ ንግድ ምርቶች ከአስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ በታች ሆነው በተገኙት ላይ እርምጃ የሚወሰድበት ስርአት መኖሩን በተመለከተ፤**

104. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ ምርቶች ከአስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ በታች ሆነው በተገኙት ላይ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

105. ይሁን እንጂ የአስገዳጅ ደረጃዎች ማስፈጸሚያ ማሻሻያ አዋጅ፣ የአሰራር ማንዋል በተቀመጠለት ጊዜ ውስጥ ተጠናቆ ጸድቆ ተግባራዊ አለመደረጉን፤ የቁጥጥር ስራው ከዚህ ቀደም በኢትዮጲያ የጥራትና ደረጃዎች ባለስልጣን ይሰራ በነበረበት የአሰራር ስርዓት የቀጠለ መሆኑን፤ አዳዲስ ዘመናዊ አሰራርና የቁጥጥር ስርዓት አለመዘርጋቱን፤ የአንዳንድ ምርቶች አስገዳጅ ደረጃ ያልወጣላቸው መሆኑን ለምሳሌ የተፈጥሮ ሙጫ እና ቅመማ ቅመም፤ በርበሬ... በመኖራቸውን የጥራት መጓደል እንዲኖር ማድረጉን፤ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

106. በናሙና ያነጋገርናቸው ላኪዎች አንዳንድ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃዎች መስፈርት ግልጽ አለመሆኑን ለምሳሌ፡- ቅመማቅመም ለውሳኔ አሰጣጥ አስቸጋሪ በመሆኑ ለማጣራት በሚደረገው ሂደት ተገልጋዩ ተጨማሪ የመጋዘን ኪራይ ለመክፈል መገደዱን ገልፀዋል፡፡

107. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው የአስገዳጅ ደረጃዎች ማስፈጸሚያ አዋጅ በተለያየ ጉዳዮች የዘገየ ቢሆንም በፌዴራል ጠቅላይ አቃቢ ህግ አስተያየት ከዳበረ በኋላ እንዲጸድቅ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ተልኳል፡፡ ግልጽ ያልሆኑ አንዳንድ አስገዳጅ ደረጃዎች ከደረጃዎች ኤጀንሲ ጋር በመሆን እንዲፈቱ ተደርገዋል፡፡ ደረጃ በጥናት ላይ ተመስርቶ የሚዘጋጅ እንደመሆኑ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምርቶች የደረጃ ዝግጅት በሂደት ላይ ይገኛሉ በማለት በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አስተያየታቸውን ገልፀዋል፡፡

108. በተጨማሪም በረቂቅ ሪፖርት ምላሽ ላይ አስገዳጅ ደረጃዎች ማስፈፀሚያ አዋጅ፣ የአሰራር ማንዋል በተቀመጠለት ጊዜ ውስጥ ተጠናቆ ተግባራዊ አለመደረጉ ትክክል ነው፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ካዘጋጀው የቆየ ቢሆንም በተለያዩ አካላት በአዋጁ ላይ በርካታ ጉዳዮችን በማንሳታቸው ጉዳዮን ማጣራት አስፈላጊ በመሆኑ የዘገየ ነው በአሁኑ ጊዜ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል በማለት ገልፀዋል፡፡

109. ምርቶች ደረጃቸውን ጠብቀው ወደ ውጭ እንዲላኩ የሚደረገው የቁጥጥር ስርአት ደካማ በመሆኑ፣ ላኪዎች በወጪ ምርት ጥራት ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ በማድረጉ ሀገሪቱ ማግኘት የሚገባትን የውጭ ምንዛሬ እንዳታገኝ ተፅእኖ ፈጥሯል፡፡

## 2.3.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ህገ-ወጥ የወጪ ንግድን የሚከታተልበት እና የሚቆጣጠርበት ስርአት የዘረጋ ስለመሆኑ፣

**የወጪ ንግድ ምርቶችን በትክክለኛ ዋጋ ስለመሸጣቸው ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት መኖሩን በተመለከተ፣**

110. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ ምርቶችን በትክክለኛ ዋጋ ስለመሸጣቸው ለማረጋገጥ የሚያስችለው ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡

111. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው መጠይቅ የቀረበላቸው ላኪዎች በሰጡት ምላሽ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ዋጋ አሳንሰው ሆነ አስበልጠው በሚልኩ ላኪዎች ላይ ክትትል በማድረግ እርምጃ የሚወሰድበት ስርአት የሌለ መሆኑን፣ወቅታዊ የዋጋ

ተመን መረጃ የማይልክላቸው መሆኑን፤ የዋጋ ተመን መረጃ የማይደርሳቸው በመሆኑ ለሽያጭ ተወዳዳሪነታቸውን የሚቀንስባቸው መሆኑን፤ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የገበያው ዋጋ መረጃ የማይደርሳቸው በመሆኑ ወቅታዊ የመላኪያ ዋጋ ባለማወቅ ውል በመግባታቸው የኮንትራት ውል የሚያፈርሱ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

112. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ጄነራል በማጠቃለያ ጥያቄ ላይ ተጠይቀው አንዳንድ ነጋዴዎች ዋጋ አሳንሰው ወደ ውጭ የሚልኩበት ሁኔታ ያለ መሆኑን፤ትክክለኛ የግብይት ስርዓት የሌለ መሆኑን፤ይህን ለመቆጣጠር ኃላፊነቱን ለብሔራዊ ባንክ እና ለንግድ ሚኒስቴር በመሰጠቱ በቅንጅት ለመስራት በሀሳብ ደረጃ ላይ ያለ መሆኑን ከኮንትራት በፊት እና በኋላ የዋጋ ቁጥጥር ያልተሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

113. በተጨምሪም በረቂቅ ሪፖርት ምላሽ ላይ ዋጋ አሳንሶም ሆነ አስበልጦ በሚልኩ ላኪዎች ላይ ክትትል በማድረግ እርምጃ የሚወሰድበት ስርአት የሌለ መሆኑ ለሚለው በዋናነት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እየተከናወነ ሲሆን ለወደፊት በትኩረት ሊሰራበት የሚገባ ጉዳይ መሆኑ ግንዛቤ ተወስዶበት ወደ ተግባራዊ እርምጃ የሚያስገባ ስርአት እየተዘረጋ ይገኛል በማለት ገልፀዋል፡፡

114. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ ምርቶችን በትክክለኛ ዋጋ ስለመሸጣቸው ለማረጋገጥ የሚያስችለው ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ባለማድረጉ ምክንያት አንዳንድ ላኪዎች ከወቅቱ የዓለም የገበያ ዋጋ በላይ በሀገር ውስጥ ምርቶችን ግዥ በመፈፀም የሀገር ውስጥ የገበያ ዋጋ እንዳይረጋጋ ተፅዕኖ መፍጠራቸው እንዲሁም የገቡትን ኮንትራት በወቅቱ እንዳይፈፅሙ እና በዝቅተኛ ዋጋ ኮንትራት (Under Invoicing) እየገቡ ምርት የሚልኩ ላኪዎች እንዲበራከቱ ምክንያት ሆኗል፡፡

**ለላኪዎች የሚሰጠው የወጪ ንግድ ፈቃድ ለተሰጣቸው አላማ መዋላቸውን የሚቆጣጠርበት ስርዓት መኖሩን በተመለከተ፤**

115. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለላኪዎች የሚሰጠው የወጪ ንግድ ፈቃድ ለተሰጣቸው አላማ መዋላቸውን የሚቆጣጠርበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

116. ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ኤክስፖርት የሚያደርጉትን ድርጅቶች ለመቆጣጠር የድርጅቶቹ አድራሻ መረጃው ተደራጅቶ ባለመያዙ በግልፅ ያለማወቅ ችግር መኖሩን እንዲሁም ለኤክስፖርት ተብሎ በማበረታቻ መልክ የሚሰጠው

ብድር ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ለማረጋገጥ ክትትል የማይደረግ መሆኑን፣ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

117. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የድህረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት በማጠቃለያ ጥያቄ ላይተጠይቀው በአብዛኛው ላኪዎችን ለመቆጣጠር አድራሻቸውን ያለማወቅ ችግር መኖሩን፤ እንዲሁም ስልክ የመቀያየርና ያለመገኘት ችግር መኖሩን፤ይህ የመቆጣጠር ስራ ግን ወደፊት ስርዓት በመዘርጋት የሚሰራ መሆኑን፤ ኤክስፖርተሩ ኤክስፖርት ማድረግ ሲጀምር ከባንክ ብድር ያገኛል በኤክስፖር (በውጪ ንግድ) ላይ አንዴ ሁለቴ ከሰራ በኋላ ብድር ተበድሮ ወደ ኢንፖርት (አስመጪ) ስራ የሚገባበት ሁኔታ መኖሩን ይህ አሰራርም ለወጪ ንግድ መዳከም እንደ አንድ ምክንያት መሆኑን፤ገልፀዋል፡፡

118. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት በሚወስዱበት ሰዓት የተወሰኑ ድርጅቶች ትክክለኛ አድራሻ ያለማስመዝገብና አድራሻ ሲቀይሩ አለማሳወቅ ችግር ያለ ሲሆን ባለው ልክ መረጃዎችን በማደራጀት ክትትል ለማድረግ እና የተሳሳተ አድራሻ በሚያስመዘግቡት ላይ እርምጃ ለመውሰድ ጥረት እየተደረገ ይገኛል በማለት በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አስተያየታቸውን ገልፀዋል፡፡

119. በተጨማሪም በረቂቅ ሪፖርት ምላሽ ላይ ኤክስፖርት የሚያደርጉትን ድርጅቶች ለመቆጣጠር የድርጅቶቹን አድራሻ መረጃው ተደራጅቶ ባለመያዙ በግልፅ ያለማወቅ ችግር መኖሩ ለሚለው የድርጅቶች መረጃ የንግድ ምዝገባና ፍቃድ በሚያወጡበት ወቅት ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ ሆኖም በመረጃው ላይ ተመስርቶ ቁጥጥር ለማድረግ የተሰጠው መረጃ አንዳንዴ ስህተት በመሆኑና ከተሰጠ በኋላ አድራሻ ለውጥ ሲደረግ ስለማያሳውቁ ችግሩን በዚህ መንገድ በመረዳት የማስተካከያ እርምጃ እየተወሰደ ይገኛል በማለት ገልፀዋል፡፡

120. ለላኪዎች የሚሰጠው የውጪ ንግድ ፈቃድ ለተሰጣቸው አላማ መዋላቸውን ለመቆጣጠር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ባለመደረጉ ላኪዎች በአነስተኛ ዋጋ ኤክስፖርት በማድረግ የኤክስፖርቱን ኪሳራ በኢምፖርት በማካካስ እየሰሩ የገበያው ዋጋ እንዳይረጋጋ ተፅእኖ ከመፍጠራቸውም በላይ ከዘርፉ ሊገኝ የሚገባውን የውጭ ምንዛሪ ገቢ እንዳይገኝ ምክንያት ሆኗል፡፡

## 2.4.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ መረጃ አያያዝ እና አሰረጫጨትን በተመለከተ ስርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ ስለመሆኑ፤

### ዘመናዊ የመረጃ አሰባሰብ፤ የመረጃ አስተዳደር እና አሰረጫጨት መመሪያ መኖሩን በተመለከተ፤

121. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ዘመናዊ የመረጃ አሰባሰብ፤ የመረጃ አስተዳደር እና አሰረጫጨት መመሪያ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

122. ይሁን እንጂ ሚ/መቤቱ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ ዘመናዊ የመረጃ አሰባሰብ፤ የመረጃ አስተዳደር እና አሰረጫጨት መመሪያ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑን፤ ታዋቂነትና ተአማኝነት ካላቸው የመረጃ ምንጮች የገበያ መረጃ ለማሠራጨት በ2008 በጀት አመት ታቅዶ እስከ 2011 በጀት አመት በሂደት ላይ በመሆኑ ወቅታዊ መረጃ ማቅረብ ያልተቻለ መሆኑን፤ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚገበያዩ ምርቶችን የአቅርቦትና የግብይት መረጃ በመቀበል፣ በማደራጀትና በማቀናበር በ2010 በጀት አመት በሣምንት፣ በወር፣ በሩብ ዓመት በምርት ዓይነት፣ አዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች በማሰራጨት ረገድ ማከናወን ያለመቻሉን፤ በዓለም ላይ የተመረተ የምርት መጠንን፣ ወቅታዊ የዓለም የገበያ ዋጋን እና የገበያ ፍላጎትን የመሳሰሉ መረጃዎችን ማግኘት የሚያስችልና የግብይት ተዋንያንን፣አምራቾች፣ ክልሎችን እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ወቅታዊ መረጃ የሚያገኙበት የገበያ መረጃ ሥርዓት አለመዘርጋቱን፣ በአንዳንድ ክልሎች ግብይቱን የሚከታተል የሰው ኃይል የተሟላ ባለመሆኑ በምርት አቅርቦትና ግብይት መረጃ ልውውጥ ላይ ክፍተት መፍጠሩን፣ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

123. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የንግድ መረጃ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በማጠቃለያ ጥያቄ ላይ ተጠይቀው እነደ ሀገር የመረጃ አያያዝ ስርዓቶች ጠንካራ ያለመሆናቸውን በመግለፅ እንደ ኤክስፖርት መረጃ ለማሰባሰብና ለማሰራጨተ የተሞከረ ቢሆንም በቂ እንዳልሆነ እና መመሪያም እንዳልተዘጋጀ፤ የንግድ መረጃ ስራ አመራር ለብቻው መስራት የተጀመረው በቅርብ ጊዜ እንደሆነ፤በከፍተኛ አመራር ትኩረት ያልተሰጠው እና በተበታተነ መልኩ የሚያዝ እንደነበር ነገር ግን እንደሀገር ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡

124. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው የመረጃ አሰባሰብ፣ አስተዳደርና አሰረጫጨት ማኑዋል በረቂቅ ደረጃ እየተዘጋጀ ሲሆን ሲፀድቅ ለወደፊቱ በተግባር ላይ ይውላል፡፡የገበያ መረጃ ሥርዓት ለመዘርጋት ከኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ጋር በቅንጅት እየተከናወነ ሲሆን የሙከራ ትግበራ ሥራ በቅርቡ ይጀምራል በማለት በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አስተያየታቸውን ገልፀዋል፡፡

125. በተጨማሪም በረቂቅ ሪፖርት ምላሽ ላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ ዘመናዊ የመረጃ አሰባሰብ፤ የመረጃ አስተዳደር እና አሰረጫጨት መመሪያ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ ለተባለው የመረጃ ስርአታችን የተበታተነ በመሆኑ እንዲሰበሰብ እና አቅም ፈጥሮ እንዲንቀሳቀስ አደረጃጀት እንዲፈጠር በማድረግ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየሰራ ይገኛል በማለት ገልፀዋል፡፡

126. ለላኪዎች ወቅታዊ መረጃ ባለመላኩ ስሌሎች ሀገራት መረጃና ልምድ በማወቅ በውጪ ንግዱ ላይ ተፎካካሪ እንዳሆኑ እንዲሁም የውጪ ምርቶችን ወቅታዊ ዋጋመረጃ ባለማግኘታቸው ምርቶችን በግምት እንዲሸጡ ከማድረጉም በላይ በተሳሳተ ዋጋ ኮንትራት በመግባት ከደንበኛ ጋር ጭቅጭቅ ውስጥ በመግባት እና የኮንትራት ውል በማፍረስ ደንበኞቻቸውን እንዲያጡ ምክንያት ሆኗል፡፡

**የላኪዎችና የገዥዎችን መረጃ (ፕሮፋይል) (አድራሻ) በየወቅቱ በማሻሻል ለላኪዎችና ለገዥዎች መሰራጨቱን በተመለከተ፤**

127. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የላኪዎችና የገዥዎችን መረጃ (ፕሮፋይል) (አድራሻ) በየወቅቱ በማሻሻል ለላኪዎችና ለገዥዎች ማሰራጨት ይኖርበታል፡፡

128. ይሁን እንጂ የገዥዎችን መረጃ ፕሮፋይል (አድራሻ) የማይልክ መሆኑን፤ ይህም ባለመደረጉ ደንበኞችን የማወቅ እንዲሁም የገበያ መዳረሻዎችን ያለማስፋት ሁኔታ መፍጠሩን፤ገዥና ሻጭ የሚገናኝበት ሁኔታ አለማወቅ ችግር መፍጠሩ፤ለደላላ ኮሚሽን ክፍያ የተጋለጡ መሆናቸውን፤ትክክለኛና ወቅታዊ የምርቶቹ ዋጋ መረጃዎች ባለመታወቁ ያለአግባብ የሆነ ኮንትራት የመፈፀም ፤ ያለአግባብ የሆነ ዋጋ መደራደር እና ምርቶች በትክክል ዋጋ እንዳይሸጡ ማድረጉን፤በናሙና ያነጋገርናቸው ላኪዎች ገልፀዋል፡፡

129. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የንግድ መረጃ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በማጠቃለያ ጥያቄ ላይ ተጠይቀው ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶችን በተመለከተ ከምርት ገበያ የዋጋ መረጃ የሚገኝ ቢሆንም ወቅቱን ጠብቆ በድህረ ገፅ እና በሌላ መልኩ ለላኪዎች በእቅደ መሰረት የማይላክ መሆኑን፤ ነገርግን መረጃ ጠይቆ ለሚመጣ ላኪ የሚሰጥ መሆኑን፤ በተጨማሪም የገዥዎች ሙሉ መረጃ ያለ ቢሆንም ለሚመለከታች (ለላኪዎች) የማይላክ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

130. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በተወሰነ ደረጃ የገዥዎች መረጃ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ከሚሲዮኖች እየተላኩልን በዘርፍ ማህበራት እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡ ሆኖም መረጃው ጥራት ላይ ችግር መኖሩና በሚፈለገው መጠንም በስፋት ስላልተሠራበት ወደፊት ሊጠናከር የሚገባው ጉዳይ ሆኖ ይገኛል በማለት በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አስተያየታቸውን ገልፀዋል፡፡

131. የላኪዎችና የገዥዎችን መረጃ (ፕሮፋይል) (አድራሻ) በየወቅቱ በማሻሻል ለላኪዎች ባለመሰራጨቱ ደንበኞቻችን በቅርበት ያለማግኘት ችግርና ገዥና ሻጭ የሚገናኝበትን ሁኔታ አለማወቅ ችግር ለደላላ ኮሚሽን መክፍልና የሀገር ገፅታ እንዲጠፋ ምክንያት ሆኗል፡፡

**የላኪዎችን የመደራደርና የመወሰን አቅም ለማጎልበት ወቅታዊና ታማኝ የሀገር ውስጥ እና የዓለም የገበያ ዋጋ ትንበያ፤ የተፎካካሪ አምራች ሀገራት የምርት ሁኔታ፣ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን ለሚመለከታቸው አካላት በየጊዜው እንዲደርሳቸው መደረጉን በተመለከተ፤**

132. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የላኪዎችን የመደራደርና የመወሰን አቅም ለማጎልበት ወቅታዊና ታማኝ የሀገር ውስጥ እና የዓለም የገበያ ዋጋ ትንበያ፤ የተፎካካሪ አምራች ሀገራት የምርት ሁኔታ፣መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን የሚመለከታቸው አካላት በየጊዜው እንዲደርሳቸው ማድረግ ይኖርበታል፡፡

133. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው ጥያቄ የቀረበላቸው ላኪዎች በሰጡት መልስ ወቅታዊና ታማኝ የሀገር ውስጥ እና የዓለም የገበያ ዋጋ ትንበያ፤ የተፎካካሪ አምራች ሀገራት የምርት ሁኔታ መረጃዎች እየተሰበሰቡና እየተነተኑ የማይላክላቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

134. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በመረጃ አቅርቦትና ሥርጭት ረገድ እጥረት ያለ ሲሆን ዋነኛ ምክንያቶችም አስተማማኝ የመረጃ ምንጭ አለመኖርና የመፈጽም አቅም አለመጎልበት ነው በማለት በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አስተያየታቸውን ገልፀዋል፡፡ በረቂቅ ሪፖርት ምላሽ ላይም ወቅታዊ ታማኝ የሀገር ውስጥ እና የአለም የገበያ ዋጋ ትንበያ፤ የተፎካካሪ አምራች አገራት የምርት መረጃዎች እየተሰበሰቡ እና እየተተነተኑ ለላኪዎች የማይላክላቸው መሆኑ የሚለው በከፊል እውነት ነው፡፡ ምክንያቱም የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን በመለየት በተወሰነ ደረጃ መረጃዎችን በማሰባሰብ የሚሰራጭ ቢሆንም በሚፈለገው ደረጃ የማድረስ ስራ በትኩረት መከናወን ይገባዋል በማለት ገልፀዋል፡፡

135. ለላኪዎች የአለም ዋጋ መረጃ እና ስሌሎች ሀገራት መረጃና ልምድ በየወቅቱ የማይደርስ በመሆኑ፤ ወደ አለም ገበያ እንዳይገቡ ከማድረጉም በላይ የምርት እጥረት ባለበት ሰዓት ምርት በወቅቱ ማቅረብ እንዳይችሉ ተፅእኖ ፈጥሯል፡፡

# ክፍል ሶስት

## መደምደሚያ

136. የውጪ ንግድ በሁለተኛ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን ለሀገሪቱ እድገት እና ልማት ካለው አስተዋፅኦ አንፃር መሰረታዊ አላማዎች እና ግቦች ከተጣለባቸው ዘርፎች መካከል አንዱ ነው፡፡በመሆኑ የውጪ ንግድ አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ እየተሰራ መሆኑ ሲገመገም የሚከተሉት ዋና ዋና ግድፈቶች ተገኝተዋል፡-

- ❖ ነባር የገበያ መዳረሻዎችን በማስፋትና አዳዲስ ገበያዎችን ሰብሮ በመግባት የኤክስፖርት አፈፃፀምን ለማሳደግ የሚያስችል የገበያ ጥናት አለመከናወኑ፤
- ❖ በኤክስፖርት እቅድ ከአቅራቢው ጀምሮ ሁሉንም የግል ሴክተሮች ተሳታፊ ያላደረገ ወይም ዕቅዱን እንዲያውቁት ያልተደረገ መሆኑን፤
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የውጪ ምርቶችን በአይነትና በመጠን ለማሳደግ የዘረጋው ስርዕት የሌለ መሆኑን፣
- ❖ በላኪ እና ገዥ ድርጅቶች መካከል የሚፈፀሙ ኮንትራቶች ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል መመሪያ ያልወጣ መሆኑ፣
- ❖ በኤክስፖርት ስራ ላይ ላኪዎች የሚገጥሟቸው ችግሮች እየተፈቱ አለመሆኑ፤
- ❖ በላኪዎች በኩል በግብይት ዕውቀት፣ ልምድና ክህሎት ውስንነት ምክንያት የመደራደር፣የመወሰን እና ኮንትራትን የማስተዳደር አቅም ማነስ መኖሩን፤
- ❖ ላኪዎች ባዘጋጁት የወጪ ንግድ ዕቅድ መሰረት ኮንትራት እንዲገቡ እና እንዲልኩ የሚደረግ ድጋፍና ክትትል የሌለ መሆኑን፤
- ❖ በተደራጀ ሁኔታ የውጪ ገበያውን ለመጠቀም የሚያስችል የድጋፍ እና ክትትል ስርአት ያልተዘረጋ መሆኑን፤
- ❖ የምርት መለያ/ብራዲንግ በቡና፤ በሰሊጥ፤ በጤፍ እና በማር ላይ በ2011 ዓ/ም የተጀመረ ቢሆንም በሌሎቹ የወጪ ምርቶች የሌለ መሆኑ፤
- ❖ የተፈጥሮ እጣን እና ሙጫ በሀገር ደረጃ የወጣለት መሰፈርትና አስገዳጅ ደረጃ የሌለ መሆኑ፣

- ❖ የአስገዳጅ ደረጃዎች ማስፈጸሚያ ማሻሻያ አዋጅ ጸድቆ ተግባራዊ አለመደረጉ፤
- ❖ ዋጋ አሳንሰውም ሆነ አስበልጠው በሚልኩ ላኪዎች ላይ ክትትል በማድረግ እርምጃ የሚወሰድበት ስርአት የሌለ መሆኑን፤
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለላኪዎች የሚሰጠው የውጪ ንግድ ፈቃድ ለተሰጣቸው አላማ መዋላቸውን የሚቆጣጠርበት ስርዓት የሌለ መሆኑን፤
- ❖ ኤክስፖርት የሚያደርጉትን ድርጅቶች ለመቆጣጠር የድርጅቶቹ አድራሻ መረጃ ተደራጅቶ ያልተያዘ መሆኑ፣
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአለም አቀፍ የንግድ ስምምነቶች ሲፈራረም የተፈራረማቸውን ስምምነቶች ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የገበያ መዳረሻዎቹንና ስምምነቶችን በተመለከተ የማያሳውቅ መሆኑን፤
- ❖ የውጪ ንግድ ማነቆዎችን ለመፍታት የመፍቻ ሥርዓት አለመኖሩ፤
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ ዘመናዊ የመረጃ አሰባሰብ፤ የመረጃ አስተዳደር እና አሰረጫጨት መመሪያ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑን፤
- ❖ የላኪዎችና የገዥዎች መረጃ (ፕሮፋይል) (አድራሻ) በየወቅቱ በማሻሻል ለላኪዎችና ለገዥዎች የማይሰራጭ መሆኑን፤
- ❖ የላኪዎችን የመደራደርና የመወሰን አቅም ለማጎልበት ወቅታዊና ታማኝ የሀገር ውስጥ እና የዓለም የገበያ ዋጋ ትንበያ፤ የተፎካካሪ አምራች ሀገራት የምርት ሁኔታ፣ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን ለሚመለከታቸው አካላት በየጊዜው የማይላክ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

137. ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሀሳቦች

138. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ እንዲሆን በሀገሪቱ የተሻለ የወጪ ንግድ አፈፃፀም እንዲኖር እና የተሻለ የውጭ ምንዛሬ ገቢ እንዲገኝ ለማስቻል ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመስራት ችግሮችን ለመፍታት ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡-

- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሌሎች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በአሁኑ ወቅት ያሉትን ነባር የገበያ መዳረሻዎችን በማጠናከርና የምርቶችን አይነት በማስፋትና አዳዲስ ገበያዎችን ሰብሮ በመግባት በመዳረሻም ሆነ የሚላከው የምርት አይነት የሚጨምርበትን ሁኔታ በመቀየስ የአገሪቱን የኤክስፖርት አፈፃፀም ለማሳደግ የሚያስችል የገበያ ጥናት በማከናወን ወደ ተግባር ሊገባ ይገባል፡፡
- ❖ በአገር አቀፍ ደረጃ በየአመቱ የሚታቀደው የኤክስፖርት እቅድ ከአቅራቢው ጀምሮ ሁሉንም የግል ሴክተሮች ተሳታፊ ያደረገ፣ ለእቅዱ ተፈጻሚነት ግብአት የሚሰጡበትንና ዕቅዱን በባለቤትነት ይዘው ለትግበራው የበኩላቸውን አስተዋጽኦ የሚያደርጉበት ሁኔታ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊያመቻች ይገባል፡፡ ይህንን በማድረግም ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶችን በአይነት፣ በብዛትና በጥራት ለማሳደግ የሚያግዝ አሳታፊ የሆነ እቅድ ሊዘጋጅ እና ለተፈጻሚነቱ ድጋፍ፣ ክትትል እና ቁጥጥር የሚያደርግበትን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ❖ በአገሪቱ ውስጥ በወጪ ንግድ ላይ የተሰማሩ ላኪዎች ምርቶቻቸውን ለመላክ በላኪ እና ገዥ ድርጅቶች መካከል የሚፈፀሙ ኮንትራቶች ላይ የላኪዎቹም ሆነ የአገሪቱ ጥቅም መጠበቁን ለማረጋገጥ የሚያግዝ የህግ ማዕቀፍ እና ህጉን ለማስፈጸም የሚረዱ እና የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል መመሪያ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ ሊያወጣ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ይህንንም በማድረግ እና የተፈጠሩትን ምቹ ሁኔታዎችን ተጠቅመው በተደራጀ ሁኔታ የውጪ

ገበያውን ለመጠቀም ላኪዎች ባዘጋጁት የወጪ ንግድ ዕቅድ መሰረት ኮንትራት እንዲገቡ እና እንዲልኩ ድጋፍና ክትትል ሊያደረግ ይገባል፡፡

- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአገሪቱ ምርቶችን ከህገወት ንግድ ለመከላከል እና በቀላሉ ለመለየትና ለማስተዋወቅ የሚያስችል ወደ ውጭ አገር የሚላኩ የሀገሪቱ ምርቶች መለያ የንግድ ምልክት (ብራዲንግ) ያላቸው የበለጠ እንዲተዋወቁ የሌላቸው ደግሞ እንዲኖራቸው ለማድረግ ከሚመለከታቸው የመንግስትም ሆነ መንግስታዊ ካልሆኑና ከግል ድርጅቶች ጋር በቅንጅት የሚሰራበትን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ❖ ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶችን ጥራት ለማስጠበቅ እና የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ ለማሳደግ እንዲረዳ በፈቃደኝነት ላይ ተመስርተው የሚሚሉ የምርት የጥራት ደረጃዎች /አስገዳጅ ደረጃ የሌላቸው/ የወጪ ምርቶች በጥናት ላይ የተመሰረተ ወደ አስገዳጅ ደረጃ ሊወጣላቸው እና ጥራታቸው የሚረጋግጥበት ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡


- ❖ በረቂቅ ደረጃ ላይ ያለው የአስገዳጅ ደረጃዎች ማስፈጸሚያ ማሻሻያ አዋጅ፣ ለሚመለከተው አካል ቀርቦ እንዲጸድቅ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ትኩረት ሰጥቶ ክትትል ሊያደርግና አዋጁ ቶሎ እዲጸድቅ የበኩሉን ጥረት ሊያደርግ ይገባል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞው አዋጁን ለማፈጸም የሚያግዙ የአሰራር ማንዋል ዝግጅት ሊከናወንና አዋጁ ከጸደቀ በኋላ ማንዋሉንም በማጽደቅ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል።

- ❖ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ሲባል ዋጋ አሳንሰው ሆነ አስበልጠው በሚልኩ ላኪዎች ላይ ክትትል በማድረግ ግልጽነትና ተጠያቂነት በሚያሳይ መልኩ እርምጃ የሚወሰድበት ስርአት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለላኪዎች የሚሰጠው የወጪ ንግድ ፈቃድ ለተሰጣቸው አላማ መዋሉን ለመቆጣጠር የሚያስችል ስርዓት ሊኖር ይገባል፡፡ ይህንን ለመከታተል የሚያስችል ኤክስፖርት የሚያደርጉትን ድርጅቶች ለመከታተልና ለመቆጣጠር የድርጅቶቹ አድራሻ መረጃ ተደራጅቶና በየጊዜው ወቅታዊ እየተደረገ በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በሌሎች አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች ሊያዝ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአለም አቀፍ የንግድ ስምምነቶች ሲፈራረም የተፈራረማቸውን ስምምነቶች ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የገበያ መዳረሻዎቹንና ስምምነቶችን በተመለከተ የሚያሳውቅበት ስርአት ሊኖረው ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድን ለማስፋፋት እንዲረዳው የሌሎች ሀገሮችን ልምድ ለመቅሰም የሚያስችሉ ጥናቶች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ሊያጠና፣ የወጪ ንግድ ማነቆዎችን ሊለይና የሚፈቱበትን መንገድ ሊያመቻችና ተግራዊ የሚደረግበት ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ የተጠኑት ጥናቶችን ለሚመለከታቸው አካላት ለላኪዎች ጭምር ሊያሰራጭና እንዲያውቁት ሊያደርግ ይገባል፡፡
- አጠቃላይ የአገሪቱን የወጪ ንግድ መረጃን ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ ዘመናዊ የመረጃ አሰባሰብ፤የመረጃ አስተዳደር እና አሰረጫጨት ሥርዓት ዘርግቶ መ/ቤቱም ሆነ በወጪ ንግድ ላይ የተሰማሩ ባለድርሻዎች ተግባራዊ ሊያደርጉት ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአገሪቱ በወጪ ንግድ ላይ የተሰማሩ የላኪዎችንና የገዥዎችን መረጃ (ፕሮፋይል) (አድራሻ) የመረጃ ቋት (ዳታ ቤዝ) ሊያዘጋጅና መረጃዎቹንም በየወቅቱ በማሻሻል ለተጠቃሚዎች ምቹ በሆነ መልኩ አደራጅቶ ሊይዝና መረጃዎችንም በመተንተን ውጤቱን ለሚመለከታቸው አካላት ሊያሰራጭ ይገባል፡፡


በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት ንግድ እና እንዱስትሪ ሚኒስቴርመ/ቤት እና በናሙና የታዩ ድርጅቶች የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በኦዲቱ ወቅት ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

# አባሪ-1 የቀድሞው ንግድ ሚኒስቴር ድርጅታዊ መዋቅር



# አባሪ-2 የወጪ ንግድ ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት ጀነራል የአሰራር ስርአት ስዕላዊ መግለጫ

## (System Description)



# አባሪ-3 የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት *(Evaluative Criteria)* |
|---|---|
| 1. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የውጪ ንግድን ለማሳደግ ባለድረሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ እቅድ አዘጋጅቶ ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን መገምገም፤ | 1.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የውጪ ንግድ ለማስፋፋት የሚያስችል ስትራቴጂክ ዕቅድ እና ፕሮግራሞችን በመንደፍ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ |
| | 2.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የውጪ ገበያ መዳረሻዎችን ለመለየት የሚያስችሉ ጥናቶች ሊያካሂድ ይገባል፡፡ |
| | 3.ሚ/ር መ/ቤቱ የጂቲፒ ሁለት እና የስትራቴጂክ ዕቅዱን መሰረት በማድረግ አመታዊ ዕቅድ ሊያዘጋጅ ይገባል |
| | 4.ሚ/ር መ/ቤቱ አመታዊ የውጪ ንግድ እቅድ ሲያዘጋጅ በውጭ ንግድ ላይ ባድርሻ የሆኑ የተለያዩ የመንግስትና የግል ባለድርሻ አካላትን ሊያሳትፍ ይገባል፡፡ |
| | 5.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሀገሪቷን የውጪ ምርቶችን ለማስተዋወቅ ማሳያ ማዕከል ማደራጀት ይኖርበታል፡፡ |
| | 6ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወደ ውጪ የሚላኩ ምርቶችን በአይነትና በመጠን የሚያድግበትን ሥርዓት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 7. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በውጪ ንግድ ዙሪያ በላኪና ገዥ ድርጅቶች መካከል የሚፈፀሙ ኮንትራቶች ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል መመሪያ በማውጣት አፀድቆ ተግበራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| | 8.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ ለማስፋፋት የንግድ አካዳሚ ማቋቋም ይኖርበታል፡፡ |
| | 9.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ ዕድገትን ለማፋጠን የሚረዱ ፖሊሲዎችን ለመንደፍ የሚያስችሉ የመነሻ ሀሳቦችን (ጥናት) ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | 10.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ እንዲስፋፋ የውጪ ንግድ ግንኙነቶችን ለመመስረት የሚያስችለው ስርአት ከሚመለከታቸው የመንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 11.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የውጪ ንግድ ስምምነቶችን የሚፈራረምበት እና የሚያስፈፅምበት ስርአት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | 12.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ በላቀ ደረጃ ለማስፋፋት የሌሎች ሀገሮችን ልምድ ለመቅሰም ጥናቶች ሊያከናውን ይገባል፡፡ |
| | 13..ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለወጪ ንግድ ማነቆ የሆኑ ችግሮች ጥናት በማከናወን ሊለዩ ይገባል፡፡ |
| **1.1.ሚኒስቴር መ/ቤቱ በውጪ ንግድ ላይ ለሚሳተፉ አካላት ድጋፍ፤ ክትትል እና የጥራት ቁጥጥር የሚያደርግበት ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፤** | 14.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ ምርቶችን የሚልኩ ላኪዎች በአለም ገበያ በስፋት ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ድጋፍ እና ክትትል የሚያደርግበት ስርአት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ (የምክር አገልግሎት፤ዓመታዊ የቢዝነስ ፕላን እንዲያዘጋጁ ወዘተ..) |
| | 15.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ምርቶችን በማስተዋወቅ |

| | |
|---|---|
| | ለላኪዎች ምቹ የገበያ ትስስር ከተለያዩ አገራት ጋር እንዲፈጠር ሁኔታዎችን ሊያመቻች ይገባል፡፡ |
| | 16.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የውጪ ንግድ ለማጠናከር ከላኪዎችና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የውይይት መድረክ ሊኖረው ይገባል፡፡ |
| | 17.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ላኪዎች ባዘጋጁት የወጪ ንግድ ዕቅድ መሰረት ምርታቸውን በማምረት ኮንትራት እንዲገቡ እና እንዲልኩ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ |
| | 18.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወደ ውጭ አገር የሚላኩ የሀገሪቱ ምርቶች በዓለም ገበያ ታዋቂ እንዲሆኑ መለያ የንግድ ምልክት (ብራዲንግ) እንዲኖራቸው ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 19.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ወደ ውጪ የሚላኩ ምርቶችን ጥራታቸውን የጠበቁ መሆናቸው የሚረጋገጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 20.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የውጪ ንግድ ምርቶች ከአስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ በታች ሆነው በተገኙት ላይ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ |
| **1.2.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ህገ-ወጥ የውጪ ንግድን የሚከታተልበት እና የሚቆጣጠርበት ስርአት የዘረጋ መሆኑን መገምገም፤** | 21..ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ ምርቶችን በትክክለኛ ዋጋ ስለመሸጣቸው ለማረጋገጥ የሚያስችለው ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡ (ምንጭ፡- የንግድ ሚኒስቴር አዋጅ 916/2009) |
| | 22..ሚኒስቴር መ/ቤቱ የውጪ ንግድ ምርቶችን ከወቅታዊ የመላኪያ ዋጋ አሳንሰው ወይም አስበልጠው በሚልኩ ላኪዎች ላይ ክትትል በማድረግ እርምጃ መውሰድ |

| | |
|---|---|
| | ይኖርበታል፡፡ |
| | 23.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ውል ገብተው ምርት ተልኮላቸው ለመረከብ ፍቃደኛ ያልሆኑ ተቀባዮች ላይ በገቡት ኮንትራት መሰረት ህጋዊ እርምጃ መወሰዱን የሚያረጋግጥበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | 24.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለላኪዎች የሚሰጠው የውጪ ንግድ ፈቃድ ለተሰጣቸው አላማ መዋላቸውን የሚቆጣጠርበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| 2.የሚኒስቴር መ/ቤቱ የውጪ ንግድ መረጃ አያያዝ እና አሰረጫጨት በተመለከተ ስርዓት መኖሩን እና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፤ | 25.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሀገሪቱን የወጪ ንግድ መረጃዎች የሚሰበስብበት፣ የሚለዋወጥበት፣ የሚያደራጅበት እና ለሚመለከታቸው አካላት የሚያሰራጭበት ስርአት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 26.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ዘመናዊ የመረጃ አሰባሰብ፤ የመረጃ አስተዳደር እና አሰረጫጨት መመሪያ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 27.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የላኪዎችና የገዥዎችን መረጃ (ፕሮፋይል) (አድራሻ) በየወቅቱ በማሻሻል ለላኪዎችና ለገዥዎች ማሰራጨት ይኖርበታል፡፡ |
| | 28.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የላኪዎችን የመደራደርና የመወሰን አቅም ለማጎልበት ወቅታዊና ታማኝ የሀገር ውስጥ እና የዓለም የገበያ ዋጋ ትንበያ፤ የተፎካካሪ አምራች ሀገራት የምርት ሁኔታ፣ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን የሚመለከታቸው አካላት በየጊዜው እንዲደርሳቸው ማድረግ ይኖርበታል፡፡ |

# አባሪ 4፡ መጠይቅ የቀረበላቸው ላኪዎችና የላኪ ማህበራት ስም

| ተ.ቁ | ስም |
|---|---|
| 1 | በለስ ኃ.የተ. የግመህበር |
| 2 | ጉና የንግድ ሥራኃ.የተ. የግ.ማህበር |
| 3 | ኤም.ኤስ.ኤ. የቅበትና ጥራጥሬ ኃ.የተ. የግ |
| 4 | ባህራን ትሬዲንግ ኃ.የተ. የግ |
| 5 | እስጢፊኖስ መከሻ አስመጪና ላኪ |
| 6 | ዳውንት ቢዝነስ ኃ.የተ. የግ |
| 7 | ደጀን ገ/መስቀል በርሄ ለኪ |
| 8 | ዛብሎን ትሬድንግ ኃ.የተ. የግ |
| 9 | አምባሰል ትሬዲንግ ኃ.የተ. የግ |
| 10 | የኢትዮጵያ ጥራጥሬ ቅባት አህሎች እና ቅመማቅመም አዘጋጅቶ ላኪዎች ማህበር |
| 11 | ኮማ አስመጪና ላኪ ኃ.የተ. የግ |
| 12 | ሳሙሄል ብርሃነ ሀጎስ አስመጪና ላኪ |
| 13 | በላይነህ ክንዴ አስመጪና ላኪ |
| 14 | ኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ፕሮዱሰር ኤክስፖርተርስ |
| 15 | እንዱት እንዱስትሪል ኃ/የተ/የግል ማህበር |
| 16 | ጃሚላ አስመጪ እና ላኪ |
| 17 | ፀሀይ ሀዱሽ ገ/ኪዳን ላኪ |
| 18 | ያለሙ አስመጪ እና ላኪ |